ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 6 ታህሣሥ 2015 ዓ.ም

## ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መንግስት “በሌብነት ላይ የጀመረውን ዘመቻ” አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታወቁ

በኢትዮጵያ ውስጥ በቅርብ ጊዜ እየተፈጠሩ ያሉ አጀንዳዎች እና ነውጦች፤ መንግስት “በሌብነት ላይ የጀመረውን” ዘመቻ እንዲያቆም የሚደረጉ መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ተናገሩ። መንግስት ሙስናን ለመታገል የጀመረውን ዘመቻ አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ይህን ያስታወቁት በወላይታ ሶዶ ከተማ የተገነባ የዱቄት እና ዳቦ ፋብሪካ ምርቃት ላይ ባደረጉት ንግግር ነው። መንግስታቸው ሌብነትን ለመታገል በመነሳቱ፤ “ዋልታ የረገጡ ቡድኖችን” በመጠቀም “ኢትዮጵያን የማመስ” ተግባራት መከናወናቸውን አስረድተዋል።

ከውስጥምሆነከውጭያሉአካላትለእነዚህኃይሎች “የፋይናንስ ድጋፍ” በመስጠት፣ “የሚያስተባብራቸውን ጉልበት” እንዲያገኙ እንዳደረጓቸው አብይ ገልጸዋል። “ሌብነት ሩቅ አይደለም፣ ጉያችን ስር ነው ያለው:: ጉያችን ስር ያለው ሌብነት እነማንን ቢያስተባብር፤ ትኩረታችንን፣ ስራችንን ለማጨናገፍ እንደሚችል ያውቃል። አሁን የምታዩት ነውጥ ሁሉ ‘የሌብነት ዘመቻው ይቁም’ የሚል ነው” ሲሉ ተደምጠዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ መንግስታቸው በሙሰኞች ላይ እርምጃ መውሰድ እንደሚጀምር በመጀመሪያ ያስታወቁት ከሶስት ወር ገደማ በፊት ከወጣቶች ጋር በአዲስ አበባ ባደረጉት ውይይት ላይ ነበር። ባለፈው ህዳር ወር መጀመሪያ ላይ ደግሞ በሙስና ላይ የሚከፈተውን ዘመቻ የሚያስተባብር ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋሙን ይፋ አድርገዋል።

የፍትህ ሚኒስትሩ ዶ/ር ጌዲዮን ጢሞቲዮስ፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተመስገን ጥሩነህ የተካተቱበት ሰባት አባላት ያሉበት ይህ ብሔራዊ ኮሚቴ፤ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም የሙስና ተዋንያን የሚለይ እና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ



መሆኑን በወቅቱ ተገልጿል። ይህንኑ ተከትሎም፤ ተመሳሳይ ኃላፊነት የተጣለባቸው ክልላዊ ኮሚቴዎች በክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ተቋቁመው ወደ ስራ መግባታቸው ተነግሯል።

ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ በወላይታ ሶዶ ከተማ የተገነባ የዱቄት እና ዳቦ ፋብሪካ ምርቃት ላይ ንግግራቸው “ኢትዮጵያ ሌብነትን በፍጥነት እና በኃይል ካልተዋጋች በስተቀር ብልጽግናዋን ልታረጋግጥ አትችልም። ብልጽግና ካልተረጋገጠ ደግሞ የተራበ 120 ሚሊዮን ዜጋ ሆኖ ሀገሩን ሊጠብቅ፣ ሊታደግ አይችልም” ሲሉ በሙስና ላይ የተጀመረው ዘመቻን አስፈላጊነት አስረድተዋል። “ዜጎቻችንን ለማብላት ስንል አብዝተን ልማት ላይ እንሰራለን፤ አብዝተን ሌብነትን እንጠየፋለን” ሲሉም አክለዋል።

“ኢትዮጵያ የሌብነት ዘመቻዋን አጠናክራ ካልቀጠለች፤ በሌላ መንገድ የሚገጥማት ፈተና በሌብነቱም ስለሚገጥማት፤ ሌብነት መታገልን አጠናክረን እንቀጥላለን” ሲሉ አብይ የመንግስታቸውን

ጠቅላይ ሚኒስትር ... ወደ ገጽ 2 የዞረ

ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅም አውለዋል የተባሉ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ሠራተኞች ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ታዘዘ

ገጽ 2

ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ አመኔታ እንዲኖራቸው ከሙስናና ብልሹ አሰራር ነጻ ሊሆኑ ይገባል — አፈ ጉባኤ ፋጤ ሰርሞሎ

ገጽ 4

ብሔራዊ ስጋት የሆነውን ሙስና በዘላቂነት ለመከላከል ከዘመቻ ባለፈ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ ሙሁራን ገለፁ

ገጽ 5

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአዲስ አደረጃጀት የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚቴ 127 ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ ጥቆማዎችን ማሰባሰብ መቻሉን አስታወቀ

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመውን የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ማቋቋማቸው ይታወቃል ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ሁለት ንዑሳን ኮሚቴዎች ያሉት ሲሆን፣ የኮሚሽኑን አጠቃላይ ወቅታዊ የስራ እንቅስቃሴ በሚመለከት ለሚዲያ አካላት መግለጫ የሰጡት የኮሚቴው ሰብሳቢና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ሊዲያ ግርማ ንዑሳን ኮሚቴ ተደርገው የተደራጁት የህግና የምርመራ ንዑስ ኮሚቴና የጥቆማና መረጃ ንዑስ ኮሚቴ መሆናቸውን አስረድተዋል ።

እንደ ሰብሳቢዋ ማብራሪያ የተጠቀሱት ሁለት ንዑሳን ኮሚቴዎችን አደራጅቶ በይፋ ተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረ ግዜ አንስቶ 127 ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ የሙስና ጥቆማዎችን ከሕዝብ ማሰባሰብ መቻሉን ገልጸዋል ።

ከ127 ከሕዝብ የተሰበሰቡ ጥቆማዎች መካከል 64 የሚሆኑትን በፍጥነት በመለየትና የክስ መዝገብ በማደራጀት ለሕግና ምርመራ ንዑስ ኮሚቴ መመራቱን ጨምሮ 37 ጥቆማዎች ላይ በቂ መረጃ በማሰባሰብ የክስ መዝገብ የማደራጀት ሥራ መሰራት መቻሉንም በመግለጫው ወቅት ሰብሳቢዋ ወ/ሮ ሊዲያ ግርማ ተናግረዋል ።

በቀሪዎቹ ከሕዝብ የተሰበሰቡ የሙስና ጥቆማዎች ላይም መረጃና ማስረጃ እንዲሁም የክስ መዝገብ የማደራጀት ስራ በዘላቂነት በንዑሳን ኮሚቴዎች በኩል እየተከናወነ የሚገኝ መሆኑንም ጨምረው ያብራሩት ሰብሳቢዋ አጠቃላይ መረጃ የማሰባሰብና የክስ መዝገብ የማደራጀት ስራዎች ከፌደራል ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ መሆኑን በመግለጫቸው ወቅት ጠቁመዋል።

እየተደረገ ባለው መረጃ የማሰባሰብ ሂደት እስካሁን እየመጡ ያሉ ጥቆማዎች የሚበረታቱና የተጀመረውን የፀረ-ሙስና ትግል የሚያጠናክሩ ናቸውም ያሉት የኮሚቴው ሰብሳቢና የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊዋ፣ የከተማችን ነዋሪዎች በዘላቂነት በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች የተደራጁ የጥቆማ መስጫ ሳጥን አገልግሎትን ጨምሮ በተመረጡ ወሳኝ ተገልጋይ በሚበዛባቸው የሴክተር ተቋማት ለአብነት ያክል በመሬት፣ በወሳኝ ኩነት፣ በንግድ፣ በገቢዎችና በሌሎችም መሰል መስሪያ ቤቶች በተዘጋጁ የጥቆማ መስጫ ሳጥኖች እንዲሁም በነጻ የስልክ መስመር 9977 ጥቆማ መስጠት የሂደቱ ተባባሪ እንዲሆን ጥሪ ማቅረቡን ከአዲስ አበባ ከንቲባ ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።



# “ሙስናን ለመከላከል መገናኛ ብዙሀን ወንጀለኞችን የማጋለጥ ስራን በልዩ ትኩረት ሊሰሩ ይገባል”፡- ዶ/ር ለገሰ ቱሉ

ሙስና ወይም ሌብነትን ለመከላከል መገናኛ ብዙሀን ወንጀለኞችን የማጋለጥ ስራን በልዩ ትኩረት እንዲሰሩ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚንስትር ዶ/ር ለገሰ ቱሉ አሳሰቡ።

በግዥ ስርዓት፣ በመሬት አስተዳደር እና በፍትህ ስርዓቱ ላይ የሚስተዋለው ሙስና ወይም ሌብነት ዜጎችን ለምሬት ሀገርንም ለችግር እየዳረገ ስለመሆኑም ሚንስትሩ ተናግረዋል።

ብልሹ አሰራሮች፣ ሽብርተኝነት እና አክራሪነት ኢትዮጵያ ደካማ እንድትሆን እያደረገ ነው ያሉት ሚንስትሩ፤ ይህ ችግር ለሙሰኞች እድል ፈጥሯል ብለዋል።

እነዚህን ብልሹ አሰራሮች በተለይም የሚዲያ ተቋማት ሊታገሉት እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ለዚህ ደግሞ አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

መገናኛ ብዙሀን ለእውነትና ለሀገር በመቆም በብልሹ አሰራር ውስጥ የሚሳተፉ ወንጀለኞችን የማጋለጥ ስራን በልዩ ትኩረት ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

ሀገርን እየፈተኑ ዜጎችንም ለምሬት እየዳረጉ ያሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ችግሮች የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚሰሩ ስራዎችንና ችግሮችን በውይይት ለመፍታት ለሚደረጉ ጥረቶች እንቅፋት እየሆነ እንደሆነም ሚንስትሩ ተናግረዋል።

መገናኛ ብዙሀን ውስብስብ የሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተፅዕኖ ሳይበግራቸው ብልሹ አሰራሮችን እንዲታገሉና የዴሞክራሲ ተቋማትም እንዲያግዙ ሚንስትሩ ዶ/ር ለገሰ አሳስበዋል።

የመልካም አስተዳደር እንቅፋት የሆነው ብልሹ አሠራር በመሆኑ ይህንን መታገልና ማጋለጥ የሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ዘርፉ ትልቅ የቤት ሥራ መሆኑን አጽንኦት ሠጥተው አብራርተዋል።

ለዴሞክራሲ እንቅፋት የሆኑ ብልሹ አሰራሮችን




በአንድ ላይ መታገል እንደሚያስፈልግ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ ገልፀዋል፡፡

የኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ለሁለት ቀናት ሲሰጥ በነበረው የምርመራ ጋዜጠኝነት ማጠናቀቂያ ላይ እንደገለጹት ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል መንግሥት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ሚዲያው በምርመራ ጋዜጠኝነት ሥራ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ በተለይ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት ከመቸውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛ መሆኑን የገለፁት ሚኒስትሩ፣ ሚዲያውም የመንግሥትን ፍላጎትና አቅጣጫን በሚገባ ተረድቶ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ለፀረ-ሙስና ትግሉ የምርመራ ጋዜጠኝነትን ማጠናከርና አቅም ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ ስልጠና ለመገናኛ ብዙሃን ሃላፊዎችና ጋዜጠኞች በአዳማ ከተማ የተሰጠ ሲሆን፣ በመድረኩ ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣ ሚኒስትሮችና ሚኒስትር ድኤታዎች፣ የተቋማት ኃላፊዎች መገኘታቸው ከዋልታ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።





# ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅም አውለዋል የተባሉ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ሠራተኞች ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ታዘዘ

ከሲሚንቶ ግዢ ጋር በተያያዘ ከ30 ሚሊየን በላይ ብር ለግል ጥቅም አውለዋል የተባሉ አራት የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ሠራተኞች ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ ታዘዘ።

ተከሳሾቹ- 1ኛ የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ተቋም የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ምክትል ዳይሬክተር ተስፋዬ ደሜ፣ 2ኛ በተቋሙ የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ግዢ ዋና ክፍል ኃላፊ አሸናፊ ተስፋዬ፣ 3ኛ በተቋሙ የግዢ ባለሙያ ቱጅባ ቀልቤሳ እና 4ኛ ሙስጠፋ ሙሳ ናቸው፡፡

የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ተቋም የግዢ ፍላጎት ሳይኖረው ትዕዛዝ ባልተሰጠበት እና ከተቋሙ ዕውቅና ውጪ የግዢ ባለሙያ ሆነው ሲሠሩ፣ በጥቅም በመመሳጠር በ2013 እና 2014 ዓ.ም በተለያዩ ቀናት ለተቋሙ ነው በሚል ከሁለት ፋብሪካዎች የገዙትን 29 ሺህ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ምርት ለግለሰቦች በመሸጥ ከ30 ሚሊየን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል ሲል ዐቃቤ ሕግ በክስ ዝርዝሩ ጠቅሷል፡፡

በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት ስልጣንን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል በታኅሣሥ 3 ቀን በነበረ ቀጠሮ መከሰሳቸው ይታወሳል።

ተከሳሾቹ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ቀርበው ጉዳያቸው ታይቷል።

ተከሳሾቹ ባለፈው ቀጠሮ ወንጀሉን አልፈጸምንም ሲሉ የሰጡትን የእምነት ክህደት ቃል ተከትሎ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ለመጠባበቅ የተሰየመው ችሎቱ፣ በፍርድ ቤቱ አስተዳደር በኩል ለምስክሮች መጥሪያ ባለመውጣቱ ሳይቀርቡ ቀርተዋል።

ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን በስልክ ጥሪ በማድረግ ለነገ በይደር እንደሚያቀርባቸው ለችሎቱ መግለጹን ተከትሎ ችሎቱም ምስክሮችን ለመስማት በይደር ቀጠሮ ይዟል።

ተከሳሾቹ በጤና ችግር እና ደኅንነት ስጋት ምክንያት በፌደራል ፖሊስ ጊዜያዊ ማቆያ አባሳሙኤል እንድንቆይ ይፈቀድልን ሲሉ ችሎቱን ቢጠይቁም፣ ዐቃቤ ሕግ አባሳሙኤል ጊዜያዊ የፌደራል ፖሊስ



የተጠርጣሪዎች ማረፊያ እንጂ የመደበኛ የተከሳሾች መኖሪያ እንዳልሆነ በማብራራት ተከሳሾቹ የጤና ችግር እንዳለባቸው በማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በጊዜያዊ ማቆያ ለመቆየት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም ሲል ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቱም ተከሳሾቹ ያቀረቡት አቤቱታ በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን ተከትሎ ተቀባይነት እንደሌለው በመግለጽ ወደ አዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲወርዱ አዟል ሲል ፋና ብሮድካስት በድረ ገፁ አስፍሯል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር...

አቋም አስታውቀዋል። “ብር አጭቀን ስለያዝን፣ ፌስቡክ እና ዩቲዩብ መቅጠር ስለምንችል፣ 10 እና 20 ወጣት አስታጥቀን ሰው መግደል ስለምንችል ‘የሌብነት ዘመቻው’ ይቆማል ብላችሁ የምታስቡ ግን ሞኛ ሞኞች ናችሁ” ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

ከዚህ ቀደም በሙስና ገንዘብ ለሰበሰቡ ሰዎችም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ “ቀላል” ያሉትን መፍትሔ በንግግራቸው ጠቁመዋል። “ትላንትና ተሳስታችሁ በስህተት ሰርቃችሁ ሀብት ያከማቻችሁ ሰዎች ካላችሁ፤ መፍትሔው ቀላል ነው። ብዙ ዳቦ ፋብሪካ ስለምንፈልግ፣ ብዙ ትምህርት ቤት ስለምንፈልግ፤ ፋብሪካዎቹን ከሰራችሁ ሰላም ይመጣል” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

“ብር አይምጣ አይደለም። ብር ሊመጣ ይችላል፤ በሎተሪም፣ በስጦታ፤ ያንን ብር ግን ለህዝብ ጥቅም የምናውለው ከሆነ አያጣላንም። ያ የሚገኝ ገንዘብ ለውስኪ እና ለግል ጥቅም እየዋለ፤ ‘ኢትዮጵያን በማመስ፣ ቤትን ብቻ ማደስ’ የሚያስቡ ሰዎች እንደዚህ አይነት ዘመን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ማስተናገድ ስለማንችል ዘመቻው ይቀጥላል” ሲሉም መንግስታቸው የጀመረውን የጸረ-ሙስና ዘመቻ እንደሚገፋበት ተናግረዋል ሲል ኢትዮጵያ ኢንሳይደር በማህበራ ገፁ አስፍሯል፡፡

# ሙስናን ለመከላከል የሁሉም ዜጎች የጋራ ተሳትፎ ወሳኝ ነው-- የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

የሙስና ተግባራትን ለመከላከል የሁሉንም ዜጎች የጋራ ጥረት እንደሚፈልግ የፌዴራል የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

በአንዳንድ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ እየተስተዋለ ያለውን የሙስና ተግባራት ለመከላከል የሁሉም ዜጎች የጋራ ጥረት እንደሚያስፈልግም ነው ኮሚሽኑ የገለጸው፡፡

እየተስተዋሉ ያሉትን መሰል ችግሮች ለመከላከል ዜጎች እገዛ እንዲያደርጉም ኮሚሽኑ ጥሪ አቅርቧል፡፡

የፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥናት እንዳመለከተው፤ በተለይም በአንዳንድ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወንጀሉ ከፍተኛ የህዝብ ምሬት እየፈጠረ ይገኛል፡፡

በኮሚሽኑ የስራ አመራር ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ ኮሚሽኑ በ2014 በጀት ዓመት ባካሔደው ጥናት በአንዳንድ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ህዝብን ያማረሩ የተደራጁ የሙስና ተግባራት መኖራቸው ተለይተዋል፡፡

የመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት በኮሚሽኑ ጥናት ከተካሄደባቸው ተቋማት መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውንም ነው የተናገሩት።

በመንግስት በጀት በሚካሔዱ አንዳንድ የልማት ፕሮጀክቶች ላይም በተደራጀ መልኩ የሚፈፀም የሙስና ወንጀል መኖሩን አረጋግጠናል ብለዋል።

በመንግስት በኩል ጥብቅ እርምጃ መወሰድ መጀመሩን አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ አንስተዋል።

በመሆኑም መንግስት ሙስናን ለመከላከል እያከናወነ ያለውን ጥረት በመደገፍ ረገድ ኅብረተሰቡ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

መንግሥት በየደረጃው የሚገኘውን መዋቅር በመፈተሽና አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት በሙስና ወንጀል የሚሳተፉ ተዋናዮችን እና ሌሎች ተጠርጣሪዎችን ለሕግ እያቀረበ መሆኑንም ገልፀዋል።

በጥናት የተደረሰባቸው የሙስና ወንጀል ተዋናዮች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

መንግስት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የሚያስተባብር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎች ተሳታፊዎችን የሚለይና ለሕግ እንዲቀርቡ የሚያደርግ የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ስራ መግባቱ ይታወሳል።





# የአማራ ክልል መንግስት የፀረ ሙስና ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን አስታወቀ

የአማራ ክልል መንግስት በክልሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን አስታወቀ፡፡

የክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ አቶ ገረመው ገብረፃድቅ እንዳሉት፣ የክልሉ መንግስት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለማስወገድ ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴዎች ከሰባት የክልሉ መሥሪያ ቤቶች አዋቅሮ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነትም ከዚህ በፊት በጥናት ተለይተው የቀረቡትንና ሌሎች፣ የሙስና ተዋንያንን እየለዩ ለህግ ስለመቅረባቸው መከታተል እና ለሚመለከታቸው የህግ አስከባሪ አካላት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የክልሉ መንግስት፣ የተዘረፉ የህዝብና የመንግስት ሀብቶች እንዲመለሱ ክትትል እንደሚያደርግ እና በሂደቱ የሚሳተፉ ተቋማት በሕግ በተደነገገው መሰረት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን እንደሚከታተልና ድጋፍ እንደሚያደርግ መገለጹን ከክልሉ ብልጽግና ፓርቲ ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

ሌሎች ክልልና የከተማ አስተዳደር የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አቋቁመው ወደ ስራ መግባታቸው ይታወቃል፡፡

# ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ አመኔታ እንዲኖራቸው ከሙስናና ብልሹ አሰራር ነጻ ሊሆኑ ይገባል — አፈ-ጉባኤ ፋጤ ሰርሞሎ

በደቡብ ክልል ያሉ ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ አመኔታ እንዲኖራቸው ከሙስናና ብልሹ አሰራር ነጻ ሊሆኑ እንደሚገባ የክልሉ ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ አሳሰቡ።

የደቡብ ክልል ፍርድ ቤቶች ሙስናን በተግባር የመታገያና የጥቆማ ስርዓቶች ንቅናቄ መድረክ በወላይታ ሶዶ ከተማ አካሄዷል።

መድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የክልሉ ምክር ቤት ዋና አፈ-ጉባኤ ፋጤ ሰርሞሎ እንዳሉት ፍርድ ቤቶች ከሙስና ፀድተው ገለልተኝነታቸው ሊረጋገጥና በህዝብ ዘንድ አመኔታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

በሀገር ሰላም፣ ልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን የፍትህ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ቢሆንም ዘርፉ የሙስና ተግባር እየተስተዋለበት መምጣቱን ተናግረዋል።

ችግሩ ጥቅመኞች ህግንና ህገመንግስታዊ ሥርዓትን ተከትለው ህዝብን ባለማገልገላቸው የመጣ መሆኑንም ገልጸዋል።

ፍርድ ቤቶች በህዝብ ዘንድ አመኔታ ያላቸው ተቋም እንዲሆኑ ከሙስና የፀዱና ገለልተኝነታቸው የተረጋገጠ ሊሆን እንደሚገባም አፈ-ጉባኤዋ አሳስበዋል።

እንደእሳቸው ገለጻ ባልተገባ የጥቅም ግንኙነትና ወገንተኝነት የሚሰሩ ግለሰቦችን በማጋለጥና በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማስቻል ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል።

“በተለይ ፍርድ ቤት በሙስና የተጠረጠሩ አካላት ጭምር ፍርድ የሚሰጥበት በመሆኑ ዳኞችም የሙስና ሰለባ ከሆኑ ችግሩን የከፋ ያደርገዋል” ብለዋል።

ይሄንን በአግባቡ በመገንዘብ በፍርድ ቤቶች ከህግ አግባብ ውጪ የሚሰሩ አካላትን በተቀመጠው የአሰራር







ስርዓት ተጠያቂ ለማድረግ ጠንካራ ትግል ማድረግ እንደሚገባ ወይዘሮ ፋጤ አሳስበዋል።

የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ኤርሰኖ አቡሬ በበኩላቸው “በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመግታት ሙሰኞች ተለይተው የሚጠየቁበትን ሥርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል” ብለዋል።

ሙስናና ሌብነትን በተለመደው አሰራር ብቻ መታገል የሚፈለገውን ውጤት እንደማያመጣ ጠቁመው፣ ለትግሉ የህዝብ ንቅናቄ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ገልፀዋል።

“ህብረተሰቡ፣ ዳኞች እና ሌሎች ፈፃሚዎች ሙሰኞችን ለመጠቆም የሚችሉባቸው መደበኛ የሞባይል ስልኮች፣ ነፃ የስልክ መስመር፣ የፌስቡክ አካውንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረገጽ እና የቴሌግራም መቀበያ ቁጥሮች ተደራሽ ለማድረግ ይሰራል” ብለዋል።

ህዝብን ያሳተፈ ንቅናቄ ፈጥሮ በጋራ በመስራት ሌብነትን ለማስቀረትና ፍርድ ቤቶችን ከሙስናና ብልሹ አሰራር ለመታደግ ተቋሙ በኃላፊነት እንደሚሰራም አረጋግጠዋል።

በንቅናቄ መድረኩ ላይ በደቡብ ክልል አስር ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች የሚገኙ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችና ባለድርሻ አካላት መሳተፋቸውን ከኢዜአ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# ለሙስና ወንጀል መርማሪዎችና ለአቃቢያነ ህግ አገር አቀፍ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጠ

በሙስና ወንጀል ክስና ምርመራ ላይ ለሚሰሩ ከ80 በላይ መርማሪዎችና አቃቢያነ ህግ የሙስና ወንጀሎች ምንነት፣ ክስ፣ ምርመራ እና የሙያ ሥነ-ምግባር ላይ አገር አቀፍ የአሰልጣኞች ስልጠና በሀዋሳ ከተማ ሳውዝ ስታር ሆቴል መስጠት ተችሏል፡፡





የኮሚሽኑ የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ስልጠና ስራ አስፈፃሚ አቶ ዳግም አላምረው የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ ኮሚሽኑ የሙስና ወንጀል የምርመራ እና ክስ ሂደት አቅማቸውን ለመገንባት በቀረፀው ፕሮጀክት መሰረት የሙስና ወንጀል መርማሪዎችና አቃቢያነ ህግ የተዘጋጀ የአሰልጣኞች ስልጠና መሆኑን ጠቁመው፣ ለስራቸው አስፈላጊ ስልጠና ስለሆነ በንቃት እንዲከታተሉና እንዲሳተፉ ያስገነዘቡ ሲሆን፤ ስልጠናው ስለሙስና ወንጀሎች ምንነት፣ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረት፣ አቃቤያነ ህግ ስለሚሰጡት ትዕዛዞችና ውሳኔዎች፣ ክስን መስማት፣ ይግባኝ፣ በሙስና ወንጀል የተገኘን ንብረት ስለመውረስ፣ የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደ ምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን እንዲሁም የሙስና ወንጀል ምርመራ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ከዚህ ባለፈም የሙስና ወንጀል መርማሪዎችና አቃቢያነ ህግ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችሉና ሙያው የሚጠይቀውን የሙያ ሥነ ምግባር ጠብቀው እንዲተገብሩ የሙያ ሥነ ምግባር ስልጠናም ተሰጧል።

የሙስና ወንጀልን ለመመርመር የወንጀሉን ባህሪያትና አይነት መለየት እንደሚገባ አገር አቀፍ የሙስና ወንጀል መርማሪዎችና አቃቢያነ ህግ የአሰልጣኞች ስልጠና ሲሰጡ የኮሚሽኑ የህግ ጉዳዮች ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ገልፀዋል፡፡

የሙስና ወንጀልን ከሌሎች ወንጀሎች በአፈፃፀም ስልቱ ውስብስብነት፣ የወንጀሉ ተሳታፊዎች ሁሉ ተጠቃሚዎች መሆናቸው፣ የወንጀል ፈፃሚዎች ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ የማድረግ አቅም፣ የሚያደርሰው ጉዳት ከሁሉም ወንጀሎች የከፋና ዘርፈ ብዙ መሆኑ፣ በህዝቡ ዘንድ እንደነውር አለመታየቱና ወንጀሉ ወሰን ተሻጋሪ መሆኑ ልዩ የሚያደርገው ባህሪያት መሆኑንም አቶ ገዛኸኝ ጠቁመዋል፡፡

የሙስና ወንጀል አይነቶችን በተመለከተ ዝቅተኛ ሙስና በመካከለኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚፈፀምበት፣ሙስና ከፍተኛ ገንዘብ የሚመዘበርበት ከፍተኛ የፖሊቲካና የመንግስት ባለስልጣናትና ትላልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት እና መዋቅራዊ ሙስና ህግ አውጪውን መጠቀሚያ በማድረግ እንዲሁም የእነዚህን ጉድለቶች በመደበቅ፣ በመከላከልና በመጠበቅ የሚገለጽ የሙስና ወንጀሎች መሆናቸው ከመድረኩ ተመላክቷል፡፡

እነዚህ የሙስና ወንጀል አይነቶች በአለም ብሎም በሀገራችን የሚያስከትሉት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ከባቢያዊ ጉዳቶች ከፍተኛ መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ፤ ሙስና በፈጠረባቸው ችግሮች የፈራረሱ ሀገራትም ማሳያ ናቸው፡፡

ይሄንን የችግሮች መንስኤ የሆነውን የሙስና ወንጀልን መከላከል ሀገርን ማዳን ነውና ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በጋራና በቅንጅት መስራት ይገባቸዋል በማለት ለሰልጣኞች ማብራራት ችለዋል፡፡



ስልጠናው ለአምስት ተከታታይ ቀናት በተለያዩ አሰልጣኞን የሙስና ወንጀሎች ምንነትና ክስ መመስረት፣ አቃቤያነ ህግ ስለሚሰጡት ትዕዛዞችና ውሳኔዎች፣ ክስን መስማት፣ ይግባኝ መጠየቅ፣ በሙስና ወንጀል የተገኘን ንብረት ስለመውረስ፣ የሙስና ወንጀሎች ጥቆማ አቀባበልና ወደ ምርመራ እንዲገባ ስለመወሰን እንዲሁም የሙስና ወንጀል ምርመራ ላይ ያተኮረ ስለጠና በመስጠት መጠናቀቅ ችሏል፡፡

# ሙስናን በተቀናጀ መንገድ በመከላከል የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ በልዩ ትኩረት ይሰራል--የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

የሙስና ተግባራት በተቀናጀ መንገድ በመከላከል የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ተግባር በልዩ ትኩረት እንደሚሰራ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አሰታወቀ።

የሙስናና የሌብነት ተግባራትን በተቀናጀ መንገድ በመከላከል የህግ የበላይነት የማረጋገጥ ስራ የህዝብን መሠረታዊ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች የመመለስ ጉዳይ በመሆኑ በልዩ ትኩረት እንደሚሰራበት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሃር ተናገሩ።

አምስት ተቋማትን ያካተተ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ እና ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ስራ መገባቱንም ጠቁመዋል።

ከንቲባ ከድር ጁሃር ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ እንደ አገር ሙስናና ሌብነትን ለመቆጣጠር እየተካሄዱ የሚገኙ ተግባራት በድሬዳዋ ከተማ በተጠናከረ መንገድ የሚተገበር መሆኑንም ገልፀዋል። ለዚህም በአስተዳደሩ ካቢኔ አምስት ተቋማት የተካተቱበት የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የአስተዳደሩ የስነ ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ተዋቅሮ ስራ መጀመሩን ነው የገለፁት።

ኮሚቴው በአስተዳደሩ የፍትህ፣ ፀጥታና የህግ ጉዳዮች ቢሮ የሚመራ ሲሆን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ የአስተዳደሩ ኦዲት ፅህፈት ቤት፣ የፌዴራል ዐቃቢ ህግ፣ የከንቲባ ፅህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ የተካተቱበት መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

ኮሚቴው በአስተዳደሩ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ተፅዕኖ እየፈጠረ በሚገኘው የሙስና ተግባራት እና ለሌብነት የሚያጋልጡ አሠራሮችን በመፈተሽ መሠረታዊ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በሙስናና በሌብነት ተግባራት የተዘፈቁ ሙሰኞች በህግ የማስጠየቅ ስራ ይሰራል ብለዋል።

ህብረተሰቡ ከኮሚቴው እና ከኮሚሽኑ ጋር በቅርበት በመስራት እና በመደገፍ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በተገቢው ለመመለስ እንዲሁም የህግ የበላይነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ማሳካት አለበት ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።



ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ፡ 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት፡ 9555
ድረ ገፅ፡ http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል፡ http://9555pmo.et/
ቴሌግራም፡https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

# ብሔራዊ ስጋት የሆነውን ሙስና በዘላቂነት ለመከላከል ከዘመቻ ባለፈ የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ ሙሁራን ገለፁ

ብሔራዊ የደህንነት ስጋት እየሆነ የመጣውን ሙስና በዘላቂነት ለመከላከል፤ በቅርቡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የፀረ-ሙስና ብሄራዊ ኮሚቴ አቋቁመው ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ይህ ብሄራዊ ኮሚቴ ወደ ስራ ገብቶ መውሰድ የጀመራቸውን እርምጃዎችንም አስታውቋል።

ክልሎችም መሰል ክልላዊ ኮሚቴ በማዋቀር እና አባላት በመሰየም በየራሳቸው ተንሰራፍቷል ያሉትን ሙስና ተከታትለው ለመግታት፤ ሙሰኞችንም ለፍርድ ለማቅረብ እንደሚሰሩ እየገለፁ ይገኛሉ።

ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር ቆይታ ያደረጉት በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የሕግ መምህሩ አቶ ፍሬው ካሳዬ፣ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሙስና በሀገር አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ ከመንሰራፋቱ ባለፈ የደህንነት ስጋት እየሆነ መምጣቱን ይናገራሉ፡፡

በተለይም በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሚታየው ሙስና ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን ያነሱት መምህሩ፤ በእነዚህ ተቋማት ላይ አገልግሎትን በገንዘብ መግዛት የተለመደ መሆኑን ነው የሚያነሱት።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ወርክ መምህሩ ዶክተር ኮማንደር ደመላሽ በበኩላቸው፣ ሙስና ከሽብር ድርጊት ባልተናነሰ ሁኔታ ሀገርን የማጥፋት አቅም ያለው መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አሁን ላይ በኢትዮጵያ የሚስተዋለው ሙስና ዘርፈ ብዙ ከመሆኑ በላይ በመዋቅር ትስስር እና በህገ ወጥ ሰንሰለት የሚፈጸሙ መሆኑ ችግሩን ይበልጥ አሳሳቢ አድርጎታል ነው የሚሉት፡፡

ሙስና በሀገሪቱ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል መንግስት የጀመረው እርምጃ የሚደነቅ ነው የሚሉት ምሁራኑ፤ ይሁን እንጂ በሙስና የተዘፈቁ የመንግስት የሥራ ሃላፊዎች እና ግለሰቦች ዘመቻውን እንዳያደናቅፉ በጥንቃቄ መመራት አለበት ባይ ናቸው።

ለአብነትም በትላልቅ የሙስና ወንጀሎች ላይ የተሳተፉ እና እርምጃ እንደሚወሰድባቸው የገመቱ ባለስልጣናት አይነኬ የሆኑ ሃሳቦችን በማንሳት ግጭት ለመጥመቅ እና ሀገርን ለማተራመስ ሊሰሩ እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

ይህን ችግር ለማስወገደም በሙስና የሚጠረጠሩ ዜጎች ላይ አስፈላጊውን ማስረጃ በፍጥነት በማሰባሰብ ተገቢውን እርምጃ በጊዜ መውሰድ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

ሙስናን በዘላቂነት ለማስወገድም ለሙስና የሚመቹ መዋቅሮችን፣ መመሪያዎችን እና ደንቦችን ማስተካከል እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ ከሁሉም በላይ ግን የመንግስት እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ወሳኝ መሆኑን አንስተዋል፡፡

ምሁራኑ፣ የመንግስት አገልግሎትን ከደላሎች ጋር በመመሳጠር ማህበረሰቡን ለከፍተኛ ምሬት ዳርገዋል እንዲሁም የመንግስትን ንብረት መዝብረዋል በተባሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለሕግ መቅረብ መጀመራቸው የሚበረታታ ተግባር ነው ይላሉ፡፡

ይህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተጀመረው የጸረ-ሙስና ትግል ገዢው ፓርቲም ሆነ መንግስት ችግሩን ከመረዳት ባለፈ ለተግባራዊነቱ ምን ያህል ቁርጠኛ እንደሆኑ የሚያመላክት ነው ብለዋል፡፡

በቀጣይም መንግስት በራሱ መዋቅር እና ስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦችን ጨምሮ ሁሉንም በወንጀሉ የሚጠረጠሩ ሙሰኞችን ተጠያቂ ማድረጉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል፡፡




ይሁን እንጂ ጅምር እንቅስቃሴውን ተከትሎ በከባድ ሙስና የተዘፈቁ የመንግስት ባለስልጣናት ያላቸውን መዋቅር እና ስልጣን እንዲሁም ገንዘብ ተጠቅመው መረጃ እንዳያሸሹ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ነው ያሉት ምሁራኑ፡፡

መንግስት ሙስናን ለመከላከል ያቋቋም ኮሚቴ ስኬታማ እና ተዓማኒ እንዲሆን ገለልተኛ የሆኑ አካላትን ማሳተፍ እንዳለበትም ነው የተናገሩት፡፡

የተጀመረው የሙስና ትግል ማህበረሰበ መር መሆን አለበት የሚሉት ምሁራኑ፣ ዜጎች ለሚያገኙት አገልግሎት ገንዘብ አለመስጠት እና ሙስና የሚጠይቅ ሲያጋጥም ለሚመለከተው አካል መጠቆም እንዳለባቸው ማሳሰባቸውን ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

# ኮሚሽኑ የ2015 ዓ.ም የ6 ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ አካሄደ

የኮሚሽኑ አመራሮችና ሠራተኞች የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀምን በቢሾፍቱ ከተማ ፒሊካን ሆቴል ተወያዩ።

ኮሚሽኑ ላለፉት ስድስት ወራት ለሙስና ተጋላጭ ተብለው በጥናት በተለዩ ዘርፎች በሙስና መከላከል ላይ ለ1686 ሰልጣኞች ስልጠና መሰጠቱን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱ ያመለክታል።





በሪፓርቱ አራት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣናት ረቂቅ የሥነ ምግባር ደንቦች መፅደቃቸው ተመላክቷል።

ሀገር አቀፍ የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች 22 ዘርፍ ተኮር አደረጃጀትን በመፍጠር የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ክትትል ድጋፍ መደረጉን ከመድረኩ ተገልጿል።

የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች አመራሮችና ሠራተኞችን ሀብትና ንብረት መመዝገብና ማሳወቅን በተመለከተ ከ24,600 በላይ ሀብት አስመዝጋቢዎች በኦን ላይን ያስመዘገቡ ሲሆን፣ የሀብት አስመዝጋቢዎችን መረጃ ወቅታዊ የማድረግ ስራም ተከናውኗል።



የመንግስትና የህዝብ ሀብትና ንብረትን ከመዝባሪዎች ለማዳን በተካሄደ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ስራ ከ43 ሚሊዬን ሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን የተቻለ ሲሆን 9,790 ካሬ ሜትር መሬት ለማስመለስ በፍትህ አካላት በሂደት ላይ እንደሚገኝ በሪፖርቱ ተመላክቷል።

በመድረኩ ኮሚሽኑ በግማሽ አመቱ ያከናወናቸው ሌሎች ተግባራት ቀርበው፣ ውይይት በማድረግ የጋራ መደረግ ተችሏል።

# ርዕሰ -አንቀፅ

# ብሔራዊ የፀረ- ሙስና ኮሚቴ መቋቋም ለፀረ- ሙስና ትግል የሚኖረው ፋይዳ

**አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ**

የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሀገራዊ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን መከላከልና መዋጋት ተግባርን ለመስራት ከፍተኛ ሀላፊነት የተሠጠው ተቋም ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ ባከናወነው ሠፊ ተግባር በሙስናና ብልሹ አሠራር የተነሳ በሀገሪቱ ሊከሰቱ የሚችሉ ከፍተኛ አደጋዎችን መከላከል፣ መቀነስና መታደግ ችሏል።

ሀገራችን በታሪኳ ከአብራኳ በወጡ ልጆቿ መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ጦርነት ስትታመስና ስትናቆር እየኖረች ያለች ሀገር ነች። ልጆቿ እርስ በእርሷ እንዲተላለቁ መሣሪያ የሚያቀብሉ ሀገራት መሳሪያዎችን በመሸጥ በልጽገዋል። ልጆቿ ግን ለራሳቸው ዕድገት አምርተው በሚሸጡት መሳሪያ እየተገዳደልን በርካታ ዜጎች ያለጊዜያቸው ይህችን ዓለም ተሰናብተዋል። ጦርነት ክፉ ስለሆነ የሰው ህይወት በማጥፋት ብቻ አይመለስም፣ ንብረት ያወድማል፤ ዜጎች ተረጋግተው እንዳይኖሩም ያደርጋል።

ሰዎች ወደ ጦርነት የሚገቡበት ምክኒያት ብዙ ናቸው። በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶችን የሚያስቀምጡ እንዳለ ሆኖ በአብዛኛው ግን ገቢ ፍላጋ /በሙስና/ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የአንድ አካባቢ ተወላጅ ወደ መሪነት ከፍታ ላይ ሲወጣ፣ የሌላኛው ተወላጅ ደግሞ መሪነት ለምን ለእሱ ብቻ መሆን ቻለ ስለሚል ወደ ፀብ ያመራል፤ አንደኛው ተወላጅ መልካም በመሥራት ሀገሪቱን ለማበልጸግ ሲል ሌላኛው ተወላጅ እኔስ ብሎ ስለሚያስብ የሀገሪቱን ሠላም የማስፈን ሥራን ተግቶ ይሰራል።

አንዱ የተሻለ ህይወት መምራት ሲጀምር ይህን የሚቀናው ደግሞ ሌላው ሰው እሱ ሆነ እኔ ሰው ነንና እሱ ቤተመንግስት የተንደላቀቀ ህይወት ሲመራ እያየሁ ዝም አልልም፤ እኔም ይገባኛል በሚል እሳቤ ሀገር ለማመስ ይነሳሳል፤ አንድን ሰው በሌላ ሰው ያገዳድላል፤ ሲመቸው ራሱም ይገላል፤ የሀገር ስም ያጣፋል፤ የህዝብ የሆነውን መሰረተ ልማት ያወድማል፤ ልማት እንዳይለማ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ይህን ደግሞ የሚያደርገው ሀገርን የሚመራው ተስፋ ቆርጦ ሥልጣኑን እንዲለቅ ነው፤ በሀገራችን እየሆነ ያለውም ይሄ ነው።

በመሆኑም ሀብትና ንብረት ፍለጋ የሚሻኮተው ሰው የሀገር መንግስት መኖሩን እንኳን በቅጡ የማያወቅ በህይወት መኖርን ብቻ መርህ አድርጎ መሬትን እየቆፈረ በማልማት ህይወትን የሚመራውን ገለልተኛ ህዝብን በጥይት ይገላል። ሌላኛው ደግሞ የመንግስትን ሀብትና ንብረት ዘርፎ መኖርን የሚፈልግ ነው። ሠርቶ መኖር ስለማይችል ሠርቆ መኖርን አቅዶና አልሞ ይንቀሳቀሳል።

ሙስና የሚፈጸመው የመንግስት ሀብትና ንብረት በመዝረፍ ወይም በመስረቅ ነው። ሙስና የሚፈጸመው ተባባሪዎችን በማደራጀት የመንግስት ሀብትና ንብረት ለግል ጥቅም በማዋል ነው። ሙስና በመንግስትና ህዝብ ሀብት ላይ በዓደራ የተሰጠውን ሥልጣን በመጠቀም ቤተሰብን ወይም ዘመድን መጠቀም ነው። ሙስና አንዱን በመጉዳት ሌላውን እንዲጠቀም ማድረግ ነው። ስለሆነም ሙስና ሀገርና ህዝብን የሚጎዳ በቀላሉ ሊጠፋ የማይችል አስፀያፊ ተግባር ነው።

ሙስና ጥቂቶችን ተጠቃሚ ሲያደርግ በርካቶችን በድህነት ማቅ ውስጥ እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው። ሙስና ህዝብና መንግስት እንዲቃቃሩ፣ የሀገር ሠላም እንዲደፈርስ፣ እርስ በእርስ እንዲገዳደሉ፣ መንግስት ለዜጎች መስጠት ያለበትን የመሠረተ ልማት ዝርጋታ እንዳይኖር፣ ሥራ እንዲጠፋ፣ ዋጋ እንዲጨምርና ኑሮ እንዲወደድ ወ.ዘ.ተ የሚያደርግ ነው።

በሀገራችን ሙስና የሁሉንም ቤት የሚያኳኳ በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ማህበራዊ ችግር ነው። መንግስት የህብረተሰቡን ኑሮ ለመደጎም ሲል ከውጪ የሚያስመጣው ስኳርና ዘይት ግዥ ላይ ሌቦች ለግል ጥቅማቸው በሚዘረጉት መረብ በተወደደ ዋጋ ይገዛሉ። ስኳርና ዘይት ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ከተጠቃሚዎች ሳይደርስ በሌቦች ወደ ወጪ ሀገር ይላካል። ሀገር ውስጥም ቢሆን በመንግስት ተመን መሠረት ለተጠቃሚ በአግባቡ መድረስ ሲገባው ሌቦች በኮንትሮባንድ ወስደው በናረ ዋጋ ይሸጡታል። መንግስት በድጎማ ያስመጣውን ዘይትና ስኳር በቅሸባ ወደ ሌላ ቦታ ከተሻገረ በኋላ ህብረተሰቡ የአትራፊ አትራፊ የነጋዴዎችን ዘይትና ስኳር በውድ ዋጋ በመግዛት ለመጠቀም ይገደዳሉ። በዚህም መንግስትን በህዝቡ እንዲጠላ ያደርጉታል።

የመብራት ኃይል ለማስገባት ጥያቄ ሲቀርብ ጉቦ ወይም እጅ መነሻ ካልተሰጠ በስተቀር ቆጣሪ የለም እየተባለ እንዲመላለስ ይደረጋል። በደላላ አማካኝነት ጉቦ የከፈለው ጠያቂ ቶሎ የመብራት ቆጣሪ አገልግሎት ያገኛል። መንግስት መብራት በፈረቃ ሲል ለአንዳንድ መብራት ኃይል ሠራተኞች ሰርግና ምላሽ ይሆንላቸዋል። ፈረቃን በጉቦ ይሸጡታል።

የከተማ መሬት በሌቦች ሀሰተኛ ካርታና የግንባታ ፍቃድ በማውጣት ይቸበቸባል። እዚህ ላይ መሬቱን በህገወጥ መንገድ የሚፈልገው ሰው ለመሬት አስተዳደር ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጉቦ ከፍሎ ሀሰተኛ የመሬት ካርታና የግንባታ ፈቃድ እንዲዘጋጅ በማድረግ ግንባታ ይፈጽማል፤ በሀሰተኛ መሬት ካርታ የባንክ ብድር ይወስድበታል።

አንድ ሰው በተለያየ ስም የተለያየ የንግድ ፈቃድ እንዲያወጣ ይፈቀድለታል፤ የተለያየ የንግድ ፈቃድ በተለያየ ስም የወሰደው ሰው ሀብት እያካበተ ለመንግስት የንግድ ግብር አይከፍልም። ቢከፍልም በጣም ትንሽ ይከፍላል። ከፍተኛ ግብር ከፋይ ለግብር ኦዲተር ጉቦ ከፍሎ ለመንግስት መክፈል የሚገባውን ግብር ለራሱ ያስቀራል።

ከተከሳሽና ከከሳሽ ጉቦ የሚቀበሉ ሌባ ፖሊሶች አሉባልታና ፤ ወንጀል የፈጸመ ሰው እንዲያዝ ትዕዛዝ ሲሰጥ ወንጀለኛው ጉቦ ከፍሎ እንዲሰወር ይፈቀድለታል። የፍርድ ቤት ዳኛ በጉቦ ወንጀለኛውን ነፃ ያወጣል ወይም ከፍተኛ ቅጣት ያከናንባል። ትራፊክ ፖሊስ ጥፋተኛ የሆነን አሽከርካሪን ዘረህ ና ይልና ጉቦ ተቀብሎ በነፃ ይለቃል። መንጃ ፈቃድ ሥልጠና ያልወሰደ ግለሰብ ከቤቱ ቁጭ ብሎ መንጃ ፈቃድ ያገኛል። ደንብ አስከባሪ ህገወጥ ግንባታ ሲፈጸም ማስቆም ሲገባ ጉቦ በመቀበል የግንባታ ሥራውን ያግዛል።

የሚዲያ ጋዜጠኛ በጉቦ እውነትን አዛብቶ ይዘግባል። መንግስት ተቋማት ውስጥ ጥራት የሌላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተጋነነ ዋጋ ይፈፃማሉ፤ መስክ ሳይሄዱ በመንግስት አበል ክፍያ የሚኖሩ የመንግስት ሠራተኞች በርካታ ናቸው። አንድ ቀን ትምህርት ቤት ሳይሄዱ፣ ዲግሪና ማስተርስ ያላቸው ብዙ ናቸው። በሀገራችን የሚፈጸም የሙስና ዓይነት በርካታ ስለሆነ ተዘርዝሮ አያልቅም።

በህመም ወደ ሆስፒታል የሚመጣ ተካሚ አልጋ ለማግኘት ጉቦ የሚጠየቅበት፣ መድሓኒት እንዲወሰድ ህገወጥ ፕሪስፕሪክሽን የሚያዘጋጁ፣ የመንግስትን አገልግሎት እያለና መስጠት እየቻለ የለም ብሎ ታካሚውን ወደ ግል ህክምና ማእከል የሚልኩ ሀኪሞች ሀገራችን ውስጥ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ ከተዘረዘሩት በላይ በርካታ ችግሮች ስለመኖራቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በተደጋጋሚ በየመድረኩ ያነሳሉ። እነዚህ ችግሮች ሀገርና ህዝብን እየጎዱ እንደሆነም በግልጽ ያስረዳሉ፤ ሰምቷቸው ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚንቀሳቀሰው ግን በጣም ጥቂት ሰው ነው። አንዳንድ የመንግስት ኃላፊዎች በየመድረኩ ስለሙስና ጎጅነት ያስረዳሉ፤ ነገር ግን ሙስናን ሲፈፅሙ ይስተዋላል። መንግስት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያቋቋመው በሀገሪቱ ያለው ሙስና እየተስፋፋ ስለመጣ በመሆኑ ነው። በህግ የተቋቋመው ኮሚሽን ራሱን በማደራጀት በመንግስት ተቋማት ውስጥ ስነምግባር እና ፀረ-ሙስናን የሚከታተሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች እንዲደራጁ አድርጎል። ስለሆነም ኮሚሽኑ ከ1993 ዓ/ም እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ ለተቋማት አመራርና ሠራተኞች እንዲሁም ለህብተሰቡ ሥነምግባር ማስተማር፣ በተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል፣ የሙስና ወንጀል ጥቆማዎችን መቀበል፣ መመርመር፣ ማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎች ሲሠራ ቆይቶ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የሙስና መከላከል መርህ ላይ የተመሠረተ ተግባራት ሲያከናውን ቆይቷል። በአዋጅ 668/2002 መሰረት የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በሌላ በኩል በየተቋማቱ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተቋሞቻቸውን አመራርና ሠራተኞች ሥነምግባር የማነጽ ሥራዎችን ማከናወን፣ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮችን እንዲሻሻሉ በማድረግ ሙስና መከላከል፣ የሙስና ጥቆማዎችን በመቀበል የማጣራት ወይም ለፍትህ አካላት የማስተላለፍ ተግባራት በመሥራት ይገኛሉ።

እነዚህ ሁለቱም አካላት እያሉ ሙስና ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን ይቀይራል፤ ለምን ሙስና ሊቀንስ አልቻለም የሚል የብዙ ወገኞች ጥያቄ ነው፤ ምላሹ ቀላል ነው። የተቋማት አመራርና ሠራተኞች የሙስናን አስከፊነት ከመናገር በስተቀር፣ ሙስናን ለመከላከል ወይም ራሳቸውም ከሙስና ለመታቀብ ያላቸው ዝግጁነት ደካማ መሆኑ ነው። ሙስና የሚሠራው በስምምነት ወይም በማስገደድ ነው። በስምምነት የሚፈጸም ሙስና የመንግስትንና የህዝብን ሀብት ለግል ጥቅም የሚያውሉበት ዘዴ ነው። ግዥ ሲፈጸም ጥራት የሌለው ዕቃ በመሸጥ አቅራቢው ተጠቃሚ ሲሆን፤ በተጋነነ ዋጋ ግዥ ሲፈጸም የተቋም አመራርና ሠራተኛ ይከብራል። አስገዳጅ ሲሆን ደግሞ ዜጎች የመንግስት አገልግሎት ፈልገው ሲሄዱ አገልግሎትን በሰበብ አስባቡ በማወሳሰብ ወይም አገልግሎት ሰጪውን ቁጥር በመቀነስ ተገልጋይ አገልግሎትን ለማፋጠን ጉቦ እንዲከፍል የሚገደድበት ሁኔታ በርካታ ነው። ሙስና የህብረተሰብ ነቃፌታ ከሌለው ይስፋፋል እንጅ አይቀንስም።

ሁለተኛው የተቋማት አደረጃጀትና አሠራር የዘመነ አለመሆን ነው። ያሉት የአሠራር መመሪያዎች ወቅታዊ የተደረጉ ባለመሆናቸው ሙስና ለመሥራት ምቹ ናቸው። የአሠራር ህጎች ወቅታዊ ባለመሆናቸው ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የተመቻቹ አይደሉም። አብዛኛዎቹ አገልግሎት መስጫዎች ከሰው ንክኪ ያልጸዱ ናቸው። በተቋማት ውስጥ የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ አሠራሮች ተለይተው ቁጥጥር አይደረግባቸውም። በዚህም በርካታ ዜጎች የመንግስት አገልግሎት ሲፈልጉ ጉቦ ወይም የእጅመነሻ ይጠየቃሉ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለአቋቋሙት ብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ላይ የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እያለ ለምን መቋቋም አስፈለገ የሚሉ ጥያቄዎች ሲነሱ ይስተዋላል። ዳሩ ግን በሀገራች ከላይ የተገለፁት በሙሉ በሀገራችን ሙስና የማይሠራበት ዘርፍና ተቋም የለም። የሥነምግባር ትምህርት ሥልጠና የተሰጠው ሰው በነጋተው ሙስና ሲሠራ ይስተዋላል። የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተመደቡበት ተቋም ሙስና ሲፈጽሙ ይታያል።

በመሆኑም በሀገሪቱ በየቦታውና በየተቋማቱ የህብረተሰብ ድጋፍ ያለው ሙስና በጣም በመስፋፋት ላይ ስለሆነ መንግስት ይህን ችግር ለመቀነስ ሀገር አቀፍ የፀረ ሙስና ኮሚቴ በማቋቋም ወደ ስራ መግባት ችሏል። ኮሚቴው ከተለያዩ ተቋማት ተመርጠው የተዋቀሩ ሲሆን፣ የፀረ ሙስና ትግል ላይ በመሳተፍ ኃላፊነት ለመወጣት አቅምና ብቃት ያለቸው ናቸው። ስለሆነም የተዋቀረው ኮሚቴ የሙስና ጥቆማ የሚቀበልባቸውን የዲጂታል አሠራር አስውቋል።

የፀረ-ሙስና ትግሉን በኮሚቴ የመምራት ሥራን ሌሎች ሀገራትም ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ ነበሩ። ለምሳሌ እ.ኤ.አ ዲሰምበር 30 ቀን 2002 የኬንያው ሞያ ኪባኪ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ሙስና ኬንያ ላይ በጣም እየተንሰራፋ በመምጣቱ የተወሰኑ በሥነምግባር የታነጹ የካቢኔ አባላት መርጠው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አባልነት በማዋቀር በየሳምንቱ አፈፃጸሙን በጥብቅ ክትትልና ዲስፕሊን በመገምገም የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ማድረጋቸውን የተገኙት መረጃዎች ያስረዳሉ። በዚህም በሙስና ሊጠረጠሩ የማይቻሉ በርካታ የመንግስት ኃላፊዎች የሙስና ወንጀል ተጠርጣሪ ሆነው በህግ ጥላ ሥር ከማድረጋቸው በላይ ያገኙትን ልምድ መነሻነት ጠንካራ የሆነ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲቋቋም አድርገዋል።

ስለሆነም የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉቦ እየተጠየቀ ነው፣ የመንግስት ሀብትና ንብረት በሌቦች እየተዘረፈ ነው የሚሉት የህብረተሰብ አካላት መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ጉቦ የሚጠየቁ ወይም የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሚዘርፉ አካላትን በቂና ትክክለኛ መረጃ ካለቸው ጥቆማዎችን በማቅረብ በትብብር መስራት ከቻሉ ከህዝቡ የቀረቡ ጥቆማዎች ሳይባክኑ በፍትህ ሚኒስቴርና በፌዴራል ፖሊስ እንዲመረመርና እንዲከሰስ የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነቱን ይወጣል።

የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ደግሞ የሙስና ሥጋት ባለባቸው ተቋማት የሥነምግባርና የሞራል እሴቶች ግንባታ ትምህርትን የማስፋፋት፣ የሙስና መከላከል ክህሎት ሥልጠና መስጠት፣ የተቋማት የሙስና ሥጋት ጥናት ማካሄድ፣ ደረጃን በመለየት የመከላከል ሥራ እንዲሠራ የማድረግ፣ የሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ ትክክኛነትን በማረጋገጥ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት መለየትና የጥቅም ግጭትን የመከላከል፣ የሙስና መረጃ የማመንጫት፣ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ሥራ የመሥራት፣ እንዲሁም ህብረተሰቡ በፀረ-ሙስና ትግል ላይ ሚናውን በተገቢ እንዲወጣ ንቅናቄ የመፍጠር እና የፀረ-ሙስና ትግል ዓለም አቀፍ ትብብርን ማጠናከር ሥራዎችን በንቃት ይሰራል።

ስለሆነም የፀረ ሙስና ትግሉ እንዲያጠናክር የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ትግል ኮሚቴ በሀገሪቱ እየተንሰራፋ የመጣውን ሙስና ለመከላከል ከፍተኛ ሚና ያለው ሲሆን፣ መንግስትም ይህን ማድረጉ የሙስና መከላከል ሥራው ያለውን ቁርጠኝነት በግልጽ ያሰያ መሆኑ የሚያበረታታ ነው። ስለሆነም የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ትግል ተኝቶ የነበረውን ተነቃቅቶና ጠንክሮ ወደ ሥራ እንዲገባ እገዛ የሚያደርግ አደረጃጀት መሆኑ ፋይዳው ከፍተኛ ስለሆነ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው።

# ቆይታ 

የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች የፀረ-ሙስና ተቋማት በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች መገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ ማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህበረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ሲሆን፣ የአፋር ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ይህን ዓለማ አንግቦ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ የስድስተኛ ዕትም እንግዳችን የአፋር ክልል የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብዱ ሳሊ ናቸው፡፡ የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ ከኮምሽነር አብዱ ሳሊ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች፡፡ መልካም ንባብ...

# ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመንግስት እና ለአንድ ተቋም ብቻ የሚተው ሳይሆን የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሃላፊነት መሆን እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል፡- የአፋር ክልል የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽነር አብዱ ሳሊህ

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ በአፋር ክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እየተከናወኑ ካሉ ስራዎች ባሻገር ክልላዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከተቋቋመ በኃላ ሙስናን ለመከላከልና ሙሰኞችን ተጠያቂ ለማድረግ ያላችሁ እቅስቃሴ ምን ይመስላል?

ኮሚሽነር አብዱ ሳሊህ፡- እንደኛ ክልል ከበፊትም በክልላችን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አኳይ ሰፊ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛል፤ ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከተቋቋመ በኃላም ስራውን የበለጠ በማጠናከር የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማቀጣጠል እየተቀሳቀስን እንገኛለን::

በሀገር ደረጃ የተፋፋመው የፀረ-ሙስና ትግል አፋር ክልል ላይም የተቀጣጠለ ሲሆን፤ በክልላችን የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ተቋቁሞ የሚሰራበትን አክሽን ፕላን በማውጣት ስራውን ለመጀመር በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል:: አፋር ክልል ላይ አሁን በተደራጀ መልኩ ቡድን በማደራጀት የሚፈፀም ሙስና በከፋ መልኩ ባይታይም፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በዘርፍ ለያይተን ወደ ስራ ልንገባበት እቅዳችን ጨርሰን በእርሰ መስተዳደሩ የተቋቋመው ኮሚቴ ስራውን እንዲጀምር የስራ ትዛዘዝ የተሰጠን ሲሆን በቅርቡ ወድስራ እንገባለን ብለን እናስባለን::

በተጨማሪም የህብረተሰቡን ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች ለመስራት ከቴሌ ጋር እየተነጋገርን ሲሆን፣ በቅርቡ የጥቆማ አማራጮችን ይፋ ይምናደርግ ይሆናል:: በዞን እና በወረዳ ደረጃ እስካሁን የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ማቋም ባንችልም በቀጣይ እስከታች ድረስ ለማደራጀት እንቅስቃሴ እያደረግን እንገኛለን::

በሌላ መረጃ የሀብት ማስመዝገብ አዋጁ ቢፀድቅም የሀብት ማስመለስና የምዝገባ ስራ አልተጀመረም፤ ምክኒያቱም በበጀት ባለመደገፉ ስራውን በህትመትና በአውቴሜሽን ለመቀየር ማቴሪያሎች ስለሚያስፈልጉ ክልሉ በበጀት አስደግፎ በሚቀጥለው ዓመት እንጀምራረን የሚል እቅድ አለን፤ እስከዚያው ግን ያለውን የሙስናና የሌብነት ደረጃው ምን ላይ ነው፣ በየትኛው ዘርፍ ላይ ነው ሙስና በከፋ መልኩ የሚታየው የሚለውንና ይህንን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰወችን የመለየት ስራ ጎን ለጎን እየተሰራ ይገኛል::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ኮሚሽኑ ከፍትህ አካላት፣ ከፖሊስና ከሚዲያ እንዲሁም ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር ሙስናና ብልሹ አሰራርን ከመከላከልና ስነምግባርን ከመገባት አኳያ በቅንጅት እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች ካሉ ቢገልፁልን?

ኮሚሽነር አብዱ ሳሊህ፡- በጋራ ስራዎችን ለመስራት ከፍትህ ጋር የተፈራረምን ሲሆን፤ አንዳንድ ጥቆማዎች ሲደርሰን ጥቆማው ምን አይነት እንደሆነ እና ተጨባጭ ነው አይደለም በሚል እኛ ካረጋገጥን በኋላ በጋራ የፍትህ አካላት የሚገቡበት ሂደት በማመቻቸት ስራዎችን እንሰራረን::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- እንደ ክልል ተግባራትን ስታከናውኑ የሚያጋጥሟችሁ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

**ሙስናን ከመከላከል አኳያ ሁሉም ዜጋ የዜግነት ግዴታ መወጣት አለበት፣ ምክኒያቱም ሙስና የእድገት ፀር ብቻ ሳይሆን ለአንድነታችን፣ ለማህበራዊና ለፖለቲካዊ ቀውስም ምክኒያት በመሆኑ ይህንን ብልሹ አሰራርና ሌብነትን ለመከላከል ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም የተለያዩ ዘርፎች ማለትም ኤጀሲዎችና ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማት የምንላቸው በሙሉ ከባለፈው ጊዜ በበለጠ አሁን በተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ለሚደረገው ወሳኝ ስራ የራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው**



ኮሚሽነር አብዱ ሳሊህ፡- በዋናነት ተግባራትን ስናከናውን የሚያጋጥሙን ችግሮች የህግ ማዕቀፋችን ባለመሻሻላቸው እና ከአደረጃጀትና ከአሰራር ጋር ተያይዞ ያለው አደረጃጀት በሚፈለገው ልክ የተሟላ ባለመሆኑ ብዙ የተጓደሉ የወረዳና የተቋም ቦታዎች ሊሟሉ የሚገባ ሲሆን፣ አንዳንድ ተቋማት ለጉዳዩ የተለዩ ትኩረት ሰጠው በመደገፍ በኩል ውስንነቶች እንዳሉ አይተናል፤ በአሁኑ ወቅት በመንግስት በኩል ያለው ቁርጠኝነት የተሻለ ስለሆነ እንደጥሩ አጋጣሚ በመወሰዱ ችግሩን እንፈታዋልን ብለን እናስባለን::

የ‹‹ፀረ-ሙስና›› ጋዜጣ፡- ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ከመከላከል አኳያ ከመንግስት፣ ከፍትህ አካላት፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ከህዝቡ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ምን ይጠበቃል?

ኮሚሽነር አብዲ ሳሊህ፡- ሙስናን ከመከላከል አኳያ ሁሉም ዜጋ የዜግነት ግዴታ መወጣት አለበት፣ ምክኒያቱም ሙስና የእድገት ፀር ብቻ ሳይሆን ለአንድነታችን፣ ለማህበራዊና ለፖለቲካዊ ቀውስም ምክኒያት በመሆኑ ይህንን ብልሹ አሰራርና ሌብነትን ለመከላከል ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሁም የተለያዩ ዘርፎች ማለትም ኤጀሲዎችና ሲቪክ ማህበራት እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማት የምንላቸው በሙሉ ከባለፈው ጊዜ በበለጠ አሁን በተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ለሚደረገው ወሳኝ ስራ የራሳቸውን ድርሻ መወጣት ብቻ ሳይሆን የበለጠ ውጤታማ ሁነን የምንወጣበት መንገድ ላይ ሊያግዙን ይገባል፤ እነደሚያግዙንም ደግሞ እምነት አለኝ::

በአጠቃላይ በየደረጃው ያለ አመራር ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በእየተቋሙና በሚመራው አካባቢ የተለዬ ርብርብ በማድረግ የሙስናና የስነምግባር ግድፈቶች ለይቶ በማውጣት መታገል አለባቸው:: ህብረተሰቡ ለፀረ-ሙስና ትግሉ ትኩረት በመስጠት ሰፊ ርብርብ በማድረግ አሁን ያለውን የሌብነት ድርጊት ከጎናችን በመሆን ሊታገል ይገባል የሚል መልክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ::

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የሀብት ምዝገባ ለሙስና መከላከል ያለው ፋይዳ

አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ



ሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ባይኖረውም የራስ ያልሆነን የመንግስትና የህዝብ ሀብትና ንብረት አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል የሚል  እንደሆነ የዓለም ባንክ ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

መገለጫውም ጉቦ መስጠትና መቀበል፣ መዝረፍ፣ መስረቅ፣ ማጭበርበር፣ ማዳላትና በሥልጣን አላግባብ መጠቀም የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሙስና በሀገራችን በሁሉም ተቋማት ውስጥ በሰዎች የሚሠራ አጸያፊ ተግባር ሲሆን የሀገርና የዓለም አቀፍ ችግርም ነው፡፡

ኢትዮጵያም ችግሩን ለመፍታት የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ትግል ስምምነት ሠነድ ፈርማ ወደ ትግል ከመቀላቀሏ በተጨማሪ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የሥነምግባር ትምህርት የማስተመር፣ በተቋማት ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮችን በመለየት ሙስናን የመከላከል እንዲሁም እስከ 2008 ዓ/ም ድረስ የሙስና ወንጀል ጥቆማ የመቀበል፣ የመመርመር፣ የማስቀጣትና የተመዘበረ ሀብት የማስመለስ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ቆይታለች፡፡ ከ2003 ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ የህዝብ ተመራጮች፣ ተሻሚዎችና የመንግስት ሠራተኞች ሀብትና ንብረት የመመዝገብና በተወሰነ ደረጃ የተመዘገበ ሀብት መረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ሥራ ተሠርቷል፡፡

ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ የምርመራና ክስ ሥራዎች ወደ ፌዴራል ፖሊስና የፍትህ ሚኒስቴር በመዛወሩ ኮሚሽኑ የሙስና እና ብልሹ አሠራር መከላከልን መርህ ላይ የተመሰረተ የሥነምግባርና የሙስና መከላከል ስልጠናዎችን የመስጠት፣ በመንግስት ተቋማትና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሙስና ቅነሳ ስትራቴጂን የማስተግበር እና ህብረተሰቡን በፀረ-ሙስና ትግል የማሳተፍ እንዲሁም የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የሀብት አስመዝጋቢዎችን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራዎች በውስን ደረጃ ተከናውኗል፡፡

በሌላ መልኩ የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ዕድሮች ላይ ኮሚሽኑ የማይመከታቸው ተቋማት ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የማህበራዊ ችግሮች ውስጥ የኑሮ ውድነት(የዋጋ ንረት) እና ከሥራ አጥነት ቀጥሎ ሙስና ሶስተኛ ደረጃን የያዘ አንገብጋቢ ችግር መሆኑን በ3ኛው የሙስና ቅኝት ጥናት የተረጋገጠ ሲሆን፣ በዓለም አቀፉ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል እ.ኤ.አ የ2021 ዓመታዊ የሙስና ሥጋት ደረጃ አሰጣጥ ኢትዮጵያ 39 በመቶ ነጥብ በማምጣት ከ180 ሀገራት በ87ኛ ደረጃ ላይ ናት፡፡ በዓለም ባንክ እ.ኤ.አ በ2021 ባከሄደው የሌብነት ደረጃ ኢንዴክስ ከ113 ሀገሮች በ61ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡

ኮሚሽኑ ከUNDP በትብብር ባከሄደው የሙስና ቅኝት ጥናት የሙስና ችግር በመንግስት ተቋማት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃን ይያዝ እንጅ የመጠን ልዩነት ካልሆነ በስተቀር በግሉ ዘርፍ፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ በሚዲያዎችና በመሳሳሉት ተቋማት ውስጥ ይፈጸማል፡፡ በጥናቱ በኢትዮጵያ ከፍተኛ፣ ዝቅተኛና ፖለቲካ ሙስና የሚፈጸም ሲሆን፣ ከሶስቱም የሙስና ዓይነቶች የበርካታ ዜጎች ቤትን እያንኳኳ ያለው ዝቅተኛ ሙስና ሲሆን ህዝብንና መንግስትን ከፍተኛ መቃቃር በመፍጠር ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ከፍተኛ ሙስና፥ ከፍተኛ የገንዘብ እንቅስቃሴ ባለቸው ተቋማት ውስጥ በመንግስት አመራሮችና ፖለቲካኞች የሚፈጸም ሲሆን ድርጊቱ በዕውቀትና ልምድ ባለቸው ሰዎች ስውር የሚፈጸም ስለሆነ የሀገርን ዕድገትና ብልጽግና በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ተግባር ነው፡፡

በኢትዮጵያ ለሙስና መንስኤዎች ተብለው የሚወሰዱት የሰዎች የሥነምግባርና የሞራል ዝቅጠት መኖር፣ በተቋማት ውስጥ የአደረጃጀትና የአሰራሮች ወቅታዊ አለመሆንና ለሙስና ሥራ ምቹ መሆናቸው እንዲሁም ለሙስና ድጋፍ የሚሰጡ የህብረተሰብ አካላት መኖራቸው እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በተወሰነ ደረጃ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት ሌብነትን እንደገቢ ምንጭ መጠቀም፣ የተቋማት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መላላት፣ በተቋማት የሚንቀሳቀስ ንብረት መጠን ከፍተኛ መሆን ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሀገራችን ከላይ የተገለጸው የሙስና ደረጃ ትክክል ስለመሆኑ በቂ ምክንያቶችና መረጃዎች ይቀርባሉ፡፡ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋማት የሚሄዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ጉቦ ወይም የእጅመንሻ ካልሰጡ የሚፈልጉትን አገልግሎት ለማግኘት እየተቸገሩ መሆኑን ቅሬታቸውን አምርረው ይገልጻሉ፡፡ አንዳንድ ቦታ ደግሞ የመንግስት ሀብትና ንብረት በህገወጥ መንገድ ለግለሰቦች እንዲተላለፉ ስለሚደረግ መንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እያጠ በመሆኑ መንግስት ለዜጎች መስጠት ያለበትን ፍታሃዊ የሃብት ክፍፍል ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑን  በተለያዩ ጊዜ በኮሚሽኑ የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የፈረመችው የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ትግል ስምምነት ሠነድ  ላይ ሀገራት ግልጽ የሆነ የፀረ-ሙስና ትግል ፖሊሲና ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣ ጠንካራና ጥርስ ያለው የፀረ-ሙስና ተቋማትን በማደራጃት ትግሉን እንዲያካሄዱ፣ የሙስና ጥቆማ መቀበያ ሥርዓት በመዘርጋት ሙስና በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ቀዳዳ የሚከፍቱ አሠራሮችን የመከላከል ሥራ እንዲሠራ፣ አመራሮችና ሠራተኞች ሀብትና ጥቅማቸውን እንዲያሳዉቁ በማድረግ የጥቅም ግጭት የመከላከል ሥራ እንዲሠራና ለፀረ-ሙስና ትግል ሀገራት እርስ በርስ በትብብርና በትስስር እንዲሠሩ እንዲሁም ሀገራት እርስ በርስ የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጡ  አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

በመሆኑም በተቋማት ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በመፍጠር ዜጎች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲያገኙ  ማድረግ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡ ስለሆነም ሀገራችን የተጠቀሱትን ተግባራት ከሞላ ጎደል እያከናወነች ቢሆንም የተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች ከመናገር ባለፉ ሙስና በተግባር ስለማይታገሉና ራሳቸውም የሙስና ተግባር ተዋናይ ስለሚሆኑ ችግሩ እየተባባሰ እንጂ እየቀነሰ አይገኝም፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያ በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ የመጀመሪያውን የመንግስት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 668/2002 አወጥታለች፡፡ በህጉም የመንግስት መሥሪያ ቤቶችና ልማት ድርጅቶች፣ የህዝብ ተመራጮች፣ ተሻሚዎችና የመንግስት ሠራተኞች ከተመደቡ ወይም ከተሾሙ ወይም ከተቀጠሩ በ45 ቀናት ጊዜ ውስጥ የባለቤቶቻቸውንና ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት  በታች የሆኑ ልጆቻቸውን ሀብት እንዲያሳውቁ ያስገድዳል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 ደግሞ የህዝባዊ ድርጅቶች አመራሮችና ሠራተኞችም ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ ተደንግጓል፡፡

ሀብትና ንብረታቸውን በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ያለአስመዘገቡ ሰዎች አንድ ሺ (1000) ብር ቅጣት በመክፈል በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያስመዘግቡ የሚያስገድድ ሲሆን፣ ሀብታቸውን ለማስመዝገብ ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎችን ሀብት ትክክለኛነት የማረጋገጥና በግኝት ላይ ተገቢ እርምጃ የመውሰድ ሥራ መሠራት እንዳለበት ህጉ ይደነግጋል፡፡

በአዋጁ ሀብት ከማስመዝገብ በተጨማሪ የተመዘገበ ሀብት መረጃ ትክክለኛነትን የማጣራት፣ የተመዘገበውን ሀብት ማየት ለሚፈልግ ሰው ጥያቄ ሲያቀርብ የማሳየት ግዴታ የተጣለበት ሲሆን፣ ሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ የደበቁ ስለመሆናቸው መረጃ ያላቸው ሰዎች ጥቆማ ካቀረቡና ጥቆማ የቀረበበት ግለሰብ ሀብት ትክክለኛ የተደበቀ ሀብት ስለመሆኑ በህግ አግባብ ከተረጋገጣ ጥቆማ ከቀረበበት የሀብት መጠን ላይ የ25 በመቶ ጥቅም ለጥቆማ አቅራቢ የሚሰጥ መሆኑን ህጉ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ስለሆነም ዜጎች  በሙስና ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አካብቷል ብለው የሚጠረጥሩትን የሀብት አስመዝጋቢ መረጃ በማየት ልዩነት ካለ ጥቆማን ለሥነምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በማቅረብ የጥቅሙ ተጋሪ መሆን እንደሚቻል ህጉ ስለሚደነግግ ተጠቃሚ መሆን ይቻላል፡፡

በሌለ በኩል ደግሞ የሀብት አስመዝጋቢዎች ካለቸው ቋሚ ገቢ ውጪ የሚያገኙትን ማናቸውንም ከሥራ ጋር በተያያዘ የሚያገኙትን ሥጦታዎች፣ መስተንግዶዎችና ግብዣዎችን በህግ አግባብ ላሉበት ተቋም ማሳወቅ እንዳለባቸው እንዲሁም በመንግስት ሥራ ላይ ውሳኔ የሚሰጡ አመራሮች በተቋሞቻቸው ከግል ጉዳይ የሚያያዙ ጉዳዮች ላይ ከመወሠን እንዲቆጠቡና ራሳቸውን ከዚህ ተግባር እንዲያገሉ የሚያስገድዱ ድንጋጌዎችን በአዋጁ ላይ ተካተዋል፡፡ በተጨማሪ የሀብት አስመዝጋቢ መረጃዎችን  ትክክለኛነት የማጣራት ሥራ ሲሠራ የሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የባንክ ሂሳብ ማጣራት ሲያስፈልግ ይህን ማድረግ እንደሚቻልም በአዋጅ ቁጥር 1236 /2013 ተደንግጓል፡፡

ሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራ በመሥራት የተመዘገበው ሀብት ትክክለኛ ስለመሆኑ በኦዲት የማረጋገጥ ሥራ ሀብት አስመዝጋቢ የሆኑ ሰዎች ከገቢ በላይ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አለማከበታቸውን ለማረጋገጥ ከማገዙም በላይ አንዳንድ ሀብት አስመዝጋቢ የሆኑ ሰዎች የግልና የመንግስት ሀብት በማደበላለቅ የተለየ ጥቅም ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥቅም ለማስቀረት ከፍተኛ ዕገዛ እንደሚያደርግ የተለያዩ ምሁራን ያካሄዱት የጥናት ሪፖርቶች ያመለክታል፡፡

የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራ ላይ ሀብትና ንብረት ያለአካበቱ ወይም ከደመወዝ ውጪ ሌላ ገቢ የሌላቸው አመራሮችና ሠራተኞች ለምን ሀብት እንዲያስመዘግቡ እንደሚደረግ በተደጋጋሚ ጥያቄዎች ያነሳሉ፡፡ በኢትዮጵያ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር በሁሉም ተቋም ውስጥ የመጠን ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ከተላላኪና ከጥበቃ አባላት እስከ ከፍተኛ ተቋም አመራር ድረስ ያሉት አደረጃጀቶች ውስጥ ያሉ ሰዎች በሌብነት የመሳተፍ ዕድሉ ከፍተኛ እንደሆነ በተደጋጋሚ በሙስና ላይ የተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም በተቋም ባለው አደረጃጀት የሙስና ተግባር ለመፈጸም ምቹ ሁኔታ ካለ አመራር ሆነ ሠራተኛው የሌብነት ተግባሩን ይፈጽማል፡፡

ለምሳሌ የጥበቃ አባል በር ላይ ወደ ተቋሙ ከሚመጡ እንግዶች ተሽከርካሪን ወደ ግቢ ለማስገባት ጉቦ ይቀበላል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም የተቋሙን ንብረት እንዲጠብቅ የተቀጠረው የጥበቃ አባል አሳቻ ሰዓት እየጠበቀ ንብረት ይሰርቃል፡፡ በርካታ ተገልጋይ ባለበት ተቋም ውስጥ የጥበቃ አባል ጉቦ እየተቀበለ ወረፋ ይሸጣል፣ ቢሮ ውስጥ የጽዳት ሥራ የምትሰራ ሴት ሰራተኛ ስታፀዳ ጠቃሚ መረጃ ካገኘት መረጃውን በሞባይሏ አንስታ በጉቦ ለሌላ ሰው አሰልፋ ትሸጠለች፡፡ ጸሐፊ የአለቃዋ ውሳኔዎችን በሞባይሏ በማንሳት ለባለጉዳይ በጉቦ ትሸጠለች፡፡ የሂሳብ ሠራተኛ ሠነድ በመደለዝ፣ በመሠረዝና በመቅደድ ከባለጉዳይ ጉቦ ይቀበላሉ፣ የመዝገብ ቤት ሠራተኞች የተቋሙን ማህተም እየተጠቀመ በጉቦ ሀሰተኛ የሥራ ልምድ መረጃ የመስጠት የመሳሰሉ የሙስና ወንጀሎች ይሠራሉ፡፡ ስለሆነም ሙስና በሁሉም ዘርፍ ላይ ሊሠራ ስለሚችል ሙስና የሚፈጽም ሰው ደግሞ ከገቢ በላይ በትንሹ ዋጋቸው ውድ የሆኑ ዕቃዎችን ገዝቶ ሲጠቀም፣ ከገቢ ጋር የማይመጣጠን ወጪ በማውጣት ኑሮ ሲመራ ከተስተዋለ፣ ይህን ችግር በቀላሉ በማወቅ እርምጃ መውሰድ የሚቻለው ደግሞ በቅድሚያ አለኝ የሚለውን ሀብትና ንብረት ማስመዝገብ ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይህም ዜጎች ከገቢ በላይ የሚኖሩ ሰዎችን  በማወቅ የተጣራ መረጃ ኑሯቸው ጥቆማ ካቀረቡ ለመመርመርና ለማረጋገጥ እንዲቻል ሁሉም አመራርና ሠራተኞች አሁን ያለቸውን ሀብት እንዲያስመዘግቡ ማድረግ የግዴታ ይሆናል፡፡

ሌላው የተመዘገበው ሀብት ለምን ለህዝብ ይፋ አይሆንም የሚሉ ጥያቄዎች ከተለያዩ ወገኖች ይቀርባሉ፡፡ በተለያዩ ሀገራት የተለያየ ዘዴ በመጠቀም የተመዘገበውን ሀብት ለህዝብ ይፋ እንደሚደረግ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እ.ኤ.አ 1974 ጀምሮ የሀብት ምዝገባ ሥራ የጀመሩት ሀገራት አሜሪካን ጨምሮ በርካታ የመዘገቡትን የሀብት ምዝገባ መረጃ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡ ከተወሰኑ ሀገራት በስተቀር አብዛኞዎቹ ሀገራት የሐብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራ የሚሠሩት በዲጂታል አሠራር ስለሆነ አንዳንድ ሀገራት የተመዘገበውን ሀብት በሙሉ በዲጂታል አሠራር ለህዝብ ይፋ ሲያደርጉ፣ የተወሰኑ ሀገራት ደግሞ ለሙስና ሥጋት አለበት ተብለው የተለዩ ተቋማት አመራርና ሠራተኞችን ሀብት ብቻ ለህዝብ ክፍት ያደርጋሉ፡፡ በተቋማት ውስጥም የተወሰኑ በእርጥብ (ሙስና የሚበላበት) ሥራ አካባቢ የሚሠሩና የሙስና ሥጋት አለበት ተብለው በተለዩ አደረጃጀቶች ላይ የሚሠሩ አመራርና ሠራተኞችን ሀብት

የሃብት ምዝገባ ... ወደ ገጽ 9 የዞረ

# የሃብት ምዝገባ ለሙስና መከላከል...

መረጃ ብቻ ለህዝብ ክፍት የሚያደርጉ ሀገራትም ዓለም ላይ አሉ። አንዳንድ ሀገራት ደግሞ የሀብት ምዝገባ መረጃ የሚያሳዩት ከዜጎች በሚቀርበው የጽሁፍ ጥያቄ ብቻ ነው። ይፋ የሚደረገው በኢንተርኔት ላይ በመጫን ለሁሉም ሠው ይፋ በማድረግ ወይም በሠነድ ላይ በማተም ይሆናል። ነገር ግን ይህን የተመዘገበ ሀብት ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉት የሀብት አስመዝገቢዎችን መረጃ ለህዝብ ይፋ ለማድረግ የሚያስችል በህጉ ላይ ግልጽ ድንጋጌዎችን በማስቀመጥ ነው።

በሀገራችን በአዋጁ 668/2002 አንቀጽ 12 (1ና 2) ላይ የተመዘገበ ሀብት ለህዝብ ክፍት ያደርጋል ይልና ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ላይ ደግሞ ክፍት የሚደረገው ከመረጃ ፈላጊው የጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ ከቻለ ነው ይላል። ህጉ ላይ ክፍት ያደርጋል ስለሚል ካልተሳሰትኩ ክፍት ማድረግ እና ይፋ ማድረግ የተለያዩ ናቸው የሚል ሀሳብ ስላለኝ በቀጣይ በማጥራት ለአንባቢ የሚቀርብ ይሆናል።

በዚሁ አዋጅ ላይ የቤተሰብ ሀብት ግን ለፍትህ አካላት ወይም ለኮሚሽኑ ሥራ ካልሆነ በስተቀር በሚስጥር እንደሚያዝም ይደነግጋል። ስለሆነም በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ህግ አግባብ የሀብት አስመዝገቢዎችን መረጃ ከህብረተሰብ በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት የሁሉንም አስመዝጋቢዎች ወይም የተወሰኑ የሐብት አስመዝገቢዎችን ይፋ ለማድረግ የህግ ክፍተት ስላለው ማሻሻያ ማድረግ የሚጠይቅ ይመስላል፤ በተጨማሪ የሀገራችንን የሀብት ምዝገባ አሠራር በዲጂታል አሠራር ለማድረግ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ መቀጠልና ማጠናቀቅን ይጠይቃል።

የሀብት አስመዝጋቢዎችን መረጃ ትክክለኛነት ማጣራትና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ደግሞ ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ለመከላከል ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቶች ይገልጻሉ። ስለሆነም የሀብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ሥራ በዓለም ላይ በሶስት ዓይነት ሊሠራ እንደሚችል መረጃዎች ይገልፃሉ።

የመጀመሪያው ቅድመ ማጣራት ሥራ ነው። በዚህ ሥራ ሀብት አስመዝገቢው መሙላት ያለበትን ሳይሞላ ከቀረ ወይም መሙላት የሌለበትን ሞልቶ ከሆነ ወዲያው እንዲያስተካክል የሚደረግበት አሰራር ነው። ሁለተኛው የማጣራት ሥራ የተመዘገበው ሀብት የሂሳብ ስሌት ስህተት ያለበት እንዲሁም እያንዳንዱ የተመዘገበው ሀብት ዓይነት በበቂ መረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ የሚጣራበት አሠራር ነው። ከዚህ አንፃር አንዳንድ ሀገራት የዲጂታል አሠራር ተጠቅመው የሀብት ምዝገባ የሚያካሄዱ ስለሆነ የተመዘገበውን ሀብት መረጃ ተቀብለው ከማጽደቃቸውና የምዝገባ ሰርትፊኬት ከመስጠታቸው በፊት ከተለያዩ ተቋማት ለምሳሌ ከባንኮች፣ ከኢንሹራሶች፣ ከመሬት ማኔጅመንትና አስተዳደር፣ ከትራንስፖርት ባለሥልጣንና ከመንግስት ቤቶች አስተዳደር እንዲሁም ከሠነዶች ማረጋገጫ ከመሳሰሉት ተቋማት በኦንላይ መረጃ በመጠየቅና ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ የምዝገባ ሰርትፊኬት ይሰጣሉ። ሶስተኛው አሠራር የተመዘገበው ሀብትና ንብረት የአካል ትክክለኛነትን፣ በሀብት አስመዝገቢው የተደበቀ ሀብትና ንብረት የሌለ ስለመሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነም ሀብትና ንብረት የተገኘበትን የመረጃ ምንጭ የማረጋገጥ ሥራ ላይ ዝርዝር ኦዲት በማካሄድ የሚረጋገጥ አሠራር ነው። በሀገራችን ዲጂታል አሠራር ያልተከተለው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥራ ብቻ ሳይሆን መረጃ የሚሰጡ ተቋማት የመረጃ አያያዛቸውም የዘመነ ባለመሆኑ የመጀመሪያ ማጣራት ሥራ ብቻ በመሥራት የምዝገባ ሰርቲፊኬት የሚሰጥበት አሠራር ስለሆነ የተመዘገበው የሀብት ምዝገባ መረጃ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛ ነው ለማለት አስቸጋሪ ያደርጋል። ስለሆነም የሀብት አስመዝጋቢዎች አጋጣሚውን በመጠቀም የሀብትና ንብረት መረጃዎችን የመደበቅ ወይም ወደፊት በሙስና አገኛለው በሚል ዕሳቤ የሌለውን ሀብት የማስመዝገብ ሁኔዎች ይስተዋላሉ። የማጣራቱም ሥራ በማኑዋል ስለሚከናወን ትክክለኛ የማጣራት ሥራ እየተሰራ ነው ለማለት ያስቸግራል። አንድ አመራር ከቀበሌ ወደ ወረዳ፣ ከወረዳ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ክልል እና ከክልል ወደ ፌዴራል እንዲሁም ከፌዴራል ወደ ውጪ ሀገር በሚያደጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ያስመዘገበውን ሀብት ከውጪ ሀገር አምበሳደርነት እስከ ቀበሌ መዋቅር ያፈራቸውን የሀብትና ንብረት መረጃዎችን በየደረጃው ካሉት የመንግስትና የግል መዋቅሮች መረጃዎችን በማግኘት የተመዘገበው ሀብት መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጊዜና የበጀት ወጪ የሚጠይቅ ነው። በርግጥ በሀገራችን ያሉት የሀብት አስመዝጋቢዎች በአብዛኛው ሊኖራቸው የሚችለው ሀብትና ንብረት መሬት፣ ቤት፣ ተሽከርካሪና አክሲዮን እንዲሁም ባንክ ላይ ጥሬ ገንዘብ ሊሆን ስለሚችል በእነዚህ መዋቅሮች ውስጥ መረጃዎችን የማጣራት ሥራ በክልልና በፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በትስስር መሥራት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የማጣራት ሥራውን ሊያቀለጥፍ ይችላል። ስለዚህ የግለሰብ ሀብትና ንብረት መዝጋቢ የሆኑ ተቋማት አሠራራቸውን ለማዘመን መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

የእኔ ሀብትና ንብረትን ላይ ብቻ እንዴት የመረጃ ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፤ እንዴትስ እኔ ተመረጥኩ የሚሉ የሀብት አስመዝጋቢዎች ያሉ ሲሆን፥ የሐብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ የሚሠራው በምዝገባ ተራቁጥር ቅደም ተከተል ወይም ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም የሐብት አስመዝጋቢው ያለበት ኃላፊነት ደረጃ ወይም በናሙና ምርጫ ወይም የሥራ አካባቢ ላይ ካለው የሙስና ሥጋት ወይም ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አካብቷል ወይም ያለአስመዘገበው ሀብትና ንብረት አለ በሚል በህዝብ ጥቆማ በመሳሳሉት የአንድ ሀብትና ንብረት አስመዝገቢ መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሊመረጥ እንደሚችል የዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ያመለክታሉ። ብዙን ጊዜ ግን ለሙስና ሥጋት እንዳለባቸው በተለዩ ተቋማት የሥራ ክፍሎች ወይም በህዝብ የሚቀርቡ ጥቆማዎች ወይም ሀብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ የማይሆኑ ሰዎችን የሀብት መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራ ቅድሚያ እንደሚሰጥም ጥናቶች ያመለክታሉ።

የሀብት አስመዝጋቢዎች መረጃ ትክክለኛነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ አሠራሮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። በተለይም በተቋሙ ለሚከናወኑ ሥራዎች በሚሰጠው ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በተለያየ መልኩ ከግል ጥቅም ጋር ሊያያዙ የሚችሉ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በቅድሚያ በመለየት የሚሰጡ ውሳኔዎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን ተገቢውን ክትትል የማድረግ ሥራ በሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ሊከናወን ይገባል። ስለሆነም በተቋም ውስጥ ያሉ አመራሮችና ሠራተኞች ሀብትና ጥቅማቸውን በማስመዘገብ የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ አሠራሮችን መራቃቸውን ማረጋገጥ በተቋሙ ውስጥ የሙስና ሥጋቶችን ለመቀነስ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል።

በተቋማት ውስጥ የተደራጁት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው የሚገኙ አመራሮችና ሠራተኞች ሀብታቸውን በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲያስመዘግቡና እንዲያሳድሱ የክትትል ሥራቸውን በተገቢ መንገድ ማከናወን እንዲሁም ለማስመዝገብ ፈቃደኛ የማይሆኑ አመራሮችና ሠራተኞች ተገቢውን ቅጣት በመቀጣት እንዲያስመዝግቡ ማድረግ ወይም ለመቀጣትና ለማስመዘገብ ፈቃደኛ የማይሆኑት አመራርና ሠራተኞች በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ለኮሚሽኑ በወቅቱ በሪፖርት ማሳወቅ የሚጠበቅባቸው ይሆናል።

በመጨረሻም የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ለሙስና መከላከል ምን ፋይዳ ይኖራዋል የሚለውን ማጠቃለል ያስፈልጋል። ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው ሙስና ውስብስብ በሆነ መልኩ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው ሰዎች የሚከናወን አስፀያፊ ተግባር ስለሆነ ሊወገዝ የሚገባ ነው። በተቋማት ውስጥ የሚገኘው ሀብትና ንብረት የሀገርና የሕዝብ ሀብትና ንብረት ነው። ተቋም የሚፈጠረው ለዜጎች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ ነው። ነገር ግን የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሆነ ሀብትና ንብረት በተቋም ውስጥ በጥቂት አመራርና ሠራተኞች ይዘረፋል፤ ተቋም የሚመሩ ሰዎች ለህዝብ ከመሥራት ይልቅ ቤተሰቦቻቸውን ለመጥቀም ይንቀሳቀሳሉ። ስለሆነም ተቋም ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ሀገርንና ህዝብን ባማከለ መልኩ ብቻ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ ውጭ የሚፈጸም ውሳኔ የግል ጥቅም ለማካባት የሚፈጸም ተግባር ይሆናል። ለግል ጥቅም የሚንቀሳቀሱ አመራርና ሠራተኞች ከገቢያቸው በላይ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ያካብታሉ። ይህን በህግ አግባብ ለማረጋገጥ የሚቻለው መጀመሪያ አለኝ የሚለውን ሀብትና ንብረት ማስመዝገብ ሲችል ብቻ ነው። ስለዚህ ሁሉም ሀብቱንና ንብረትን ማስመዘገብ ይኖርበታል። የተዘመገበው ሀብት ትክክል ስለመሆኑ የዲጂታል አሠራር በመተግበር ማረጋገጥና የተደበቀ ሀብትና ንብረት ላይ ለሀገርና ህዝብ ተመላሽ ሊሆን ይገባል።

## ኮሚሽኑ በተቋማት ላይ የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ ለተቋማት ምክረ ሃሳብ በመስጠት ለሙስና መከላከል የሚኖረው ፋይዳ እና የተከናወኑ ጥናቶች

ኮሚሽኑ በመንግስት ተቋማት እና በልማት ድርጅቶች እንዲሁም በሌሎች ተቋማት ሙስናና ብልሹ አሠራሮችን አስቀድሞ የመከላከል፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያደርሱትን ኪሣራ እንዲቀንስ ወይም እየተባባሰ እንዳይሄድ ለማድረግ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ ይገኛል።

የአሠራር ሥርዓት ጥናት ዋነኛው ዓላማ ለሙስናና ብልሹ አሠራሮች መከሰት ምክንያት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን መለየት እና ችግሮቹ የሚፈቱበትን መንገድ መፈለግ ነው።

በመሆኑም ኮሚሽኑ አስቸኳይ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል የማጣራት ስራውን ያካሄደው "የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ድርጅት አመራሮችና ሰራተኞች በሐምሌና ነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም መስከ ሳይወጡ የ24 ቀን ዉሎ አበል እንዲከፈላቸዉ ተደርጓል፤ አንድ የፈረንጅ ላም በተጋነነ ዋጋ ማለትም በ170 ሺህ ብር እንዲገዛ ተደርጓል፤ በ3 ሚሊዮን ብር የተገዛ ችግኝ በ6 ሚሊዮን ብር የተገዛ በማስመሰል የመንግስትን ገንዘብ ለታለመለት አላማ እንዳይዉል ተደርጓል፤ እንዲሁም የግዥ መመሪያን ያልጠበቀ የግዥ ባለሙያዎች እያሉ ሶስት ኮሚቴ በማቋቋም በ15,000,000 (አስራ አምስት ሚሊየን) ብር የሰራተኛ ካፍቴሪያ እቃ ግዥ ለ3 ዙር በማከፋፈል ለመግዛት ሂደት ላይ ሲሆን በግልጽ ጨረታ መግዛት እየተቻለ ወደ ውስን ጨረታ በመውሰድ ከአንድ ድርጅት ለመግዛት በሂደት ላይ ይገኛሉ" በሚል ለኮሚሽኑ በቀረበ ጥቆማ በመቅረቡ በተቋሙ በአካል በመገኘት ለማጣራት ስራው የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎችን በማሰባሰብ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ነው።

በዚህም መሰረት ኮሚሽኑ ባካሄደው የማጣራት ስራ የለያቸውን ግኝቶች ማቅረብ የቻለ ሲሆን፤ ተቋሙ በሰኔ ወር 2014 ዓ.ም ለሰራተኞች አዲስ ድልድል ባደረገው መሰረት የዌብ ሳይት ስልጠና እና የስትራቴጂ ዝግጅት፣ የስራ ትውውቅ እና ስልጠና (induction) በማስፈለጉ እንዲሁም የተቋሙ ሰራተኞች ከአዕምሮ ህሙማን እና ከአካል ጉዳተኞች ጋር ጊዜያቸዉን የሚያሳልፉ በመሆኑ ለማነቃቃት እና የእኔነት ስሜት እንዲኖር ለማድረግ ለተቋሙ ኃላፊዎች ከሀምሌ 1 እስከ 28 ድረስ አዳማ ከተማ በማሳተፍ የ28 ቀን አበል እንዲከፈላቸዉ መደረጉን እና ለሰራተኞች በሁለት ቡድን ከነሐሴ 1 እስከ 24 እና ከነሐሴ 5 እስከ 30 ባሉት ቀናት ዉስጥ ሆለታ ከተማ ሁለት መድረኮችን በማመቻቸት በማካሄድ የ24 ቀን ዉሎ አበል መከፈል መቻሉን እና የወተት ላሞች በመደበኛ የግዥ ስርዓት ከአቅራቢዎች ለማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከግብርና ሚኒስቴር እና ከጤና ሚኒስቴር ባለሙያዎችን በማካተት፣ ኮሚቴ በማደራጀት፣ በባለሞያዎች በማስፈተሽ፣ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ፣ ከጥናቱ ጎን ለጎን ከገበያ ዋጋ ጋር በማነጻጸር ከተለያዩ ግለሰቦች ግዥዉ በለቀማ እንዲፈፀም በማኔጅመንት ቃለጉባኤ በመያዝ የተወሰነ መሆኑን እንዲሁም የቡራዩ አዕምሮ ህሙማን ማዕከል ለህሙማን በአረንጓዴ ልማት ምቹ ለማድረግ በሰኔ ወር 2014 ዓ.ም ከጤና ሚኒስቴር በተገኘ 3.5 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ ችግኝ ተከላ ለማከናወን የዋጋ ማቅረቢያ ዘዴን ተከትሎ የችግኝ ግዥዉ የተፈፀመ መሆኑን፣ በተጨማሪም አገልግሎቱ የካፍቴሪያ መገልገያ እቃዎች እና ማብሰያ ማሽነሪዎች ለማሟላት ገበያ አስጠንቶ የግዥ ሂደቱን ቢጀምርም ባለው የገበያ ሁኔታ በተፈለገው ጥራት የሚያቀርቡ ነጋዴዎችን በብዛት ማግኘት ስላልተቻለ ተገልጋዮች በችግር ውስጥ እንደሚገኙ ገልጾ ለተገልጋይ የጦር ጉዳተኞች፣ ለሌሎች ተገልጋዮች እና ሰራተኞች የካፍቴሪያ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ለአንድ ጊዜ የቀጥታ ግዥ ለመፈጸም ልዩ ፍቃድ እንዲሰጥ የመንግስት ግዥ እና ንብረት ባለስልጣንን የተጠየቀ ቢሆንም በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲያካሂዱ የተፈቀደላቸው በመሆኑ ከአምስት ያላነሱ አቅራቢዎችን በመጋበዝ አወዳድረው በልዩ ሁኔታ ግዥ ለመፈጸም በሂደት ላይ ያለ መሆኑን ከዉይይትና ከሰነድ ማስረጃ ለመረዳት ተችሏል።

በዚህም መሰረት ኮሚሽኑ ከማጣራት ስራው ግኝት በመነሳት ለኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ድርጅት ስልጠና የተደረገባቸው እና ውሎ አበል የተከፈለባቸው ቀናት ጊዜን በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም እና የመንግስትን በጀት ለሚገባው ተግባር በቁጠባ ማዋል እንዲቻል በቀጣይ አሰራሩ እንዲስተካከል እንዲሁም የወተት ላሞችና የችግኝ ግዢ ሂደት አሰራሩን ተከትሎ እየተሰራ ያለ ቢሆንም ለተቋሙ ማህበረሰብ ስለአሰራር ሂደቱ ግልፅነትን ያላሰፈነ በመሆኑ በተቋሙ ቅሬታ የፈጠረበትን ሁኔታ በቀጣይ የአሰራር ግልጽነትን ለተቋሙ ማህበረሰብ በመፍጠር ማከናወን የሚያስፈልግ መሆኑ ትኩረት እንዲሰጠው በማለት ኮሚሽኑ የማጣራት ስራ ውጤት ምክረ-ሀሳብ መስጠት ችሏል።

በተጨማሪም ኮሚሽኑ አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናቱን ያካሄደው በኢትዮ ኢንጂነሪንግ የድንጋይ መፍጫ ለመሸጥ ባወጣዉ ጨረታ በመሳተፍ መስፈርቱን አሟልተን እያለን ያለአግባብ እንዳናልፍ ተደርገናል በሚል ለኮሚሽኑ በቀረበ ጥቆማ መነሻነት ነው።

አስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥናቱ የተከናወነው በተቋሙ በአካል በመገኘት ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና መረጃዎችን በማሰባሰብና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ሲሆን፣ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው መረጃ አቅራቢዉ ጨረታ ሰነዱን ሲመልሱ በትክክል አሽገዉ ያላስገቡ መሆኑን ነው።

በመሆኑም በተቋሙ መደበኛ ጨረታ ሰነድ የጨረታ ሰነድ ቁጥር ኢ.ኢ.ግ/ንአክ/ብግጨ001/2014 ክፍል ሁለት መመሪያ 17 የመጫረቻ ሰነድ አስተሻሸግና ምልክት አደራረግ ቁጥር 17.3 እና 17.4 ሁሉም ኢንቨሎፖች በተገቢዉ ሁኔታ መታሸግ እንዳለባቸዉና በማይለቅ ቀልም/በሰም/ምልክት መደረግ እንዳለባቸዉ ይገልፃል፤ ሆኖም ግን የመረጃ አቅራቢዉ የጨረታ ሰነድ በፕላስተር የታሸገና ምንም አይነት የሰም ምልክት ያልተደረገበት መሆኑን በተደረገዉ ምልከታ መረዳት ተችሏል።

በተጨማሪም መረጃ አቅራቢዉ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማሟላት አለባቸዉ ተብለዉ የተጠቀሱትን ሰነዶች ያላሟሉ መሆኑ ነው።

በመደበኛ የጨረታ ሰነድ የተጫራቾች መመሪያ ላይ ተጫራቾች በዘርፉ የተሰማሩበትና የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆናቸዉን እንዲሁም የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ ነጥቦች ናቸው ተብለዉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ መረጃ አቅራቢዉ ያላሟሉ መሆኑን በተደረገዉ የሰነድ ምልከታ፣ በጨረታ መክፈቻ ጊዜ በተያዘ ቃለ ጉባኤና የተጫራቾች የጨረታ ሰነድ እየተከፈተ በሚነበብበት ጊዜ በተያዘ ቼክ ሊስት ያላሟላ መሆኑን መረዳት ተችሏል።

ስለሆነም ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ኮሚሽኑ መረጃ አቅራቢው በጨረታ ሰነዱ ላይ አንድ ተጫራች ማሟላት አለበት ተብለዉ የተቀመጡትን በስራ ዘርፉ የተሰማራበትንና የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ያላሟላ መሆኑን፤ ጨረታ ሰነዱም በሚመልስበት ወቅት በአግባቡ ታሽጎና ምልክት ተደርጎበት ገቢ አለመደረጉን በተደረገው የማጣራት ሂደት ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም በሂደት ላይ የሚገኘው የሽያጭ ጨረታ ባለበት ሁኔታ ቢካሄድ የተሻለ ይሆናል በሚል ምክረ-ሀሳብ ተሰጧቸዋል።

ስለሆነም ኮሚሽኑ በተሻሻለው የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ማስተካከያ እንዲደረግ ምክረ-ሀሳብ ያቀረበ ሲሆን፣ በጉዳዩ ላይም የቅርብ ክትትል እንደሚደረግ ተገልፃል።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር



ይህ አምድ በዋናነት ትኩረት የሚያደረገው ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የማይገባ ጥቅም ለራሱ በማስገኘት ወይም ለሌላ ሰው በማስገኘት ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት በማድረስ በተሰጠዉ ኃላፊነት ከሌላ ሰው ላይ ጥቅም የተቀበለ ወይም የጠየቀ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በማስገኘት የተሰጠዉን ስልጣን ወይም የህዝብ አደራ ያላአግባብ የተገለገለ፤ ወይም ለሌላ ሰው ያስገኘ ወይም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ ለመንግስት ወይም ለህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የማይገባ ጥቅም የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም በአግባቡ ለተፈጸመ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት ልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ስራ የማይገባ ጥቅም ለማንኛውም ሰዉ የሰጠ ወይም ከማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዉ ድርጅት ሰራተኛ የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ፈጻሚነት ተጠያቂ በመሆን በምርመራ የሙስና ወንጀል ፈፅመው የተገኙ አካላት መረጃዎችን ለአንባቢያን ተደራሽ የምናደርግበት ነው፡፡

በመሆኑም ከኦሮሚያ ባንክ እና ከወጋገን ባንክ ካዝና ከ2 ሚሊዮን በላይ የኢትዮጲያ ብር እና ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦችን በመዝረፍ በከባድ ውንብድና ወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች ላይ የዓቃቢህግ ምስክር ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰጠ ሲሆን፣ ተለዋጭ ቀጠሮውን የሰጠው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት ነው፡፡

ከሁለቱ ባንኮች ካዝና የገንዘብ ዝርፊያ ፈጽመዋል ተብለው በከባድ ውንብድና ወንጀል የተከሰሱ ተከሳሾች በተለያዩ ሁለት መዝገቦች ነው ጉዳያቸው እየታየ የሚገኘው፡፡

ከኦሮሚያ ባንክ የተፈጸመ የገንዘብ ዝርፊያን በተመለከተ የተከሰሱት ሁለት ተከሳሾች ማለትም የሆቴል ባለቤት ነው የተባለው 1ኛ ተከሳሽ ይርጋለም አድማሱ እና 2ኛ ተከሳሽ አለሙ አሰፋ ናቸው፡፡

የዓቃቢ ህግ ክስ እንደሚያመላክተው ተከሳሾቹ በመስከረም 7 ቀን 2015 ዓ/ም ከምሽቱ ከ 2:00 ሰዓት እስከ 5:00 ባለው ጊዜ ውስጥ በአ/አ ከተማ በቦሌ ክ/ከ ወረዳ 7 የረር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ከሚገኝ ከኦሮሚያ ባንክ በከልቻ ቅርጫፍ ውስጥ ያልተያዘ ኤልያስ የሚባል የባንኩ ጥበቃ ሰራተኛ በዕለቱ በጥበቃ ስራ ላይ የነበረ ሌላ ጥበቃን እኔ እጠብቅልሀለው ሂድ ተኛ በማለት እንዲተኛ በማድረግ 1ኛና 2ኛ ተከሳሾችን ደውሎ በማስመጣቱ መሆኑ በክሱ ተጠቅሷል፡፡

በዚህ መልኩ ተጠርተው ከመጡ በኋላ ተከሳሾቹ ባንክ ውስጥ በመግባት ከሌሎች ያልተያዙ ግብረአበሮች በመሆን የባንኩን የገንዘብ ካዝና በፌሮ ብረት በመስበር 2 ሚሊዮን 289 ሺ 114 ብር እና 2ሺ 414 የአሜሪካ ዶላርና እንዲሁም 55 ዩሮ መዝረፋቸው በክሱ ተዘርዝሯል፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ሀ/1 እና አንቀጽ 672 /ሀ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፈው በከባድ የውንብድና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

ተከሳሾቹ ክሱ ከደረሳቸው እና በችሎት በንባብ ከተሰማ በኋላ ''ወንጀሉን አልፈጸምንም'' ሲሉ የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ከሳሽ ዓቃቢ ህግ ወንጀሉ ለመፈጸሙ የሚያስረዱ ምስክሮች ይሰሙልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት የዓቃቢህግ ምስክርን ለመስማት ለጥር 3 ቀን 2015 ዓ/ም ተለዋጭ ቀጠሮ የሰጠ ሲሆን፤ በሌላ መዝገብ ደግሞ ማለትም ከወጋገን ባንክ የገንዘብ እና ክላሽ ኮፕ መሳሪያ ዘርፈዋል በተባሉ 8 ተከሳሾች ላይ የዓቃቢህግ ምስክር ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቷል፡፡

በዚህ የወጋገን ባንክን በመዝረፍ ወንጀል ከተከሰሱ ተከሳሾች መካከል የኦሮሚያ ባንክን በመዝረፍ የተከሰሰው የሆቴል ባለቤት ነው የተባለው ይርጋለም አድማሱ የተባለው ተከሳሽ ይገኝበታል፡፡

የወጋገን ባንክን በመዝረፍ በከባድ ውንብድና ወንጀል የተከሰሱ አጠቃላይ ተከሳሾች 8 ሲሆኑ 1ኛ ተከሳሽ ገበያው ምስጋናው፣ 2ኛ እዮብ ተመስገን፣ 3ኛ የሆቴል ባለቤት ነው የተባለው ይርጋለም አድማሱ፣ 4ኛ ተሾመ ደምሴ ፣ 5ኛ ሀ/ማርያም መለሰ፣ 6ኛ ጥላሁን ወልዴ እና 7ኛ ጌታሁን ተፈራ እንዲሁም 8ኛ ተከሳሽ አቤል ንጉሴ ይባላሉ፡፡

ዓቃቢህግ ሁለት ክስ ያቀረበባቸው ሲሆን በአንደኛው ክስ ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ አምስት ተከሳሾች ላይ ብቻ የቀረበ ነው፡፡

ይህም ክስ እንደሚያመላክተው'' ገበያው ምስጋናው የተባለው አንደኛ ተከሳሽ በወጋገን ባንክ በጥበቃ ሰራተኛነት ሲሰራ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመመሳጠር በነሃሴ 3ቀን 2014 ዓ/ም ከምሽቱ 3:00 ሰዓት ላይ የዕለቱ ጥበቃ ሰራተኛን በማገትና አፉን በፕላስተር በማፈን የባንኩን የገንዘብ ካዝና በፌሮ ብረት በመስበር 409 ሺህ 172 ብር እና አንድ ክላሽ ኮፕ መሳሪያ ከ30 ጥይት ጋር ዘርፈዋል'' ሲል ዓቃቢህግ በክሱ ጠቅሷል፡፡

ሁለተኛው ክስ ደግሞ ከ6ኛ እስከ 8ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን፣ በዚህም ክስ ከላይ የተጠቀሱ በአምስት ተከሳሾች ከወጋገን ባንክ ጃክሮስ ቅርጫፍ ዘርፈዋል የተባለውን አንድ ክላሽ ኮፕ መሳሪያ ከ30 ጥይት ጋር 6ኛ ተከሳሽ ጥላሁን ወልዴ ገዝቶ ለ7ኛ ተከሳሽ ለጌታሁን ተፈሩ መሸጡ በክሱ የተጠቀሰ ሲሆን

7ኛ ተከሳሽ ደግሞ በ8ኛ ተከሳሽ አቤል ንጉሴ ደላላነት መሳሪያውን ለሌላ ላልተያዘ ግለሰብ በመሸጥ በአጠቃላይ በውንብድና ወንጀል ክስ የተከሰሱ ናቸው፡፡

እነዚህም ተከሳሾች ክሱ ከደረሳቸውና በችሎት በንባብ ከተሰማ በኋላ ''ወንጀሉን አልፈጸምንም' ሲሉ የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ፍርድ ቤቱ የዓቃቢህግ ምስክርን ለመስማት ለጥር 19 ቀን ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ያሉ ተከሳሾች በማረሚያ ቤት የሚገኙ ሲሆን 6ኛ 7ኛ እና 8ኛ ተከሳሾች ግን የ13 ሺህ ብር ዋስ አሲዘው ከስር መፈታት ችለዋል፡፡

በሌላ መረጃ በኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በአርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጅ ስም 8 ሺ 35 ካ.ሜ ስፋት ያለው የመንግስት ይዞታ ላይ ለ22 ግለሰቦች በህገ-ወጥ መንገድ የተሰጠ ካርታ እንዲፀና እና መብት በመፍጠር እና በመንግስት ላይ ከ8 ሚሊዮን ብር በላይ ጉዳት ባደረሱ የለሚኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ምክትል ሀላፊ አቶ ተስፋዬ ግርማን ጨምሮ በ43 ተከሳሾ ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረት የተቻለ ሲሆን፤ የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው፡- 1ኛ ተከሳሽ ተስፋዬ ግርማ የለሚኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ምክትል ሀላፊ እና የፕሮሰስ ካውንስል አባል፣ 2ኛ ተከሳሽ አየለ ጉቱ የወረዳ 14 አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ሀላፊ እና የአርሶ አደር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ 3ኛ ተከሳሽ ጎሳዬ ደሜጅማ የወረዳ 14 አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ሀላፊና የአርሶ አደር ኮሚቴ ጸሀፊ፣ 4ኛ ተከሳሽ በፍቃዱ ወንድወሰን፣ 5ኛ ተከሳሽ ሮባ ደበሌ፣ 6ኛ ተከሳሽ መታሰቢያ አባተ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር የአርሶ አደር ኮሚቴ አባላት፣ 7ኛ ተከሳሽ ለምለም አባይነህ እሸቴ የለሚ ኩራ ክ/ከ አስተዳደር የወረዳ 14 አስተዳደር ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ 8ኛ ተከሳሽ ልዑልሰገድ ታደሰ ደምባ በክፍለ ከተማው የሰነድ አጣሪ ባለሙያ፣ 9ኛ ተከሳሽ ጭምዴሳ ፉልዓ እና 10ኛ ተከሳሽ በቃሉ ፀደቀ የቴክኒክ ባለሙያ መሀንዲሶች፣ 11ኛ ተከሳሽ ዋሲሁን ሰውነት የመደበኛ ካርታ ዝግጅት ስራ ሂደት ሀላፊ እና የፕሮሰስ ካውንስል አባል፣ ከ12ኛ እስከ 20ኛ ተከሳሾች የይዞታው ተጠቃሚ ግለሰቦች፣ 21ኛ ተከሳሽ ሄራን ሀይሉ የወረዳ 04 አስተዳደር የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ሀላፊ እና የአርሶ አደር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ 22ኛ ተከሳሽ ናዖል ቶላ የወረዳ 04 አስተዳደር የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ እና አርሶ አደር ኮሚቴ ፀሃፊ፣ 23ኛ ተከሳሽ ፍቅሬ ጫላ፣ 24ኛ ተከሳሽ ብርሃኑ በጅጋ፣ 25ኛ ተከሳሽ ዘውዱ ሐይሌ የወረዳ 04 አስተዳደር የአርሶ አደር ኮሚቴ አባላት፣ 26ኛ ተከሳሽ ልዑል ተፈራ የወረዳ 04 አስተዳደር ጽ/ቤት ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ 27ኛ ተከሳሽ ዳዊት ከልሌ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ የቴክኒክ ጉዳዮች አጣሪና ወሳኝ ባለሙያ፣ ከ28ኛ እስከ 40ኛ ተከሳሾች የይዞታው ተጠቃሚ ግለሰቦች፣ 41ኛ ተከሳሽ ኢብራሂም ሀሰን የቴክኒክ ባለሙያ እና የፕሮሰስ ካውንስል አባል፣ 42ኛ ተከሳሽ ከፍያለው አሰፋ የይዞታ ማስተካከል ቡድን መሪ እና የፕሮሰስ ካውንስል አባል እንዲሁም 43ኛ ተከሳሽ ሀይለኢየሱስ ደስታ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት የውል ሰነዶች አጣሪ ባለሙያና የፕሮሰስ ካውንስል አባል፣ በድምሩ በ43 ተከሳሾች ላይ የእያንዳንዳቸው የተሳትፎ ደረጃ ተጠቅሶ በዐቃቤ ሕግ ሶስት ክሶች መስርቶበቸዋል፡፡

የዐቃቤ ሕግ ክስ እንደሚያስረዳው 1ኛ ክስ ላይ ከ2ኛ እስከ 20ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ የቀረበ ሲሆን ከ2ኛ እስከ 11ኛ ያሉ ተከሳሾች እንደየስራ ኃላፊነታቸው በመንግስት ሰራተኝነት እንዲሁም የአርሶ አደር ኮሚቴ አባል ሆነው በልዩ ተካፋይነት በሚያገለግሉበት ወቅት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ቀኑና ወሩ ተለይቶ ባልታወቀ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በቀድሞ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 15 በአሁኑ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ይዞታዎች ላይ ሊያከናውኗቸው የሚገባቸውን ተግባራት በአግባቡ ሳይፈፀሙ ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው ከ12ኛ እስከ 20ኛ ተከሳሾች ጋር በጥቅም በመመሳጠር ያለ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ከ12ኛ እስከ 20ኛ ለተጠቀሱት ተከሳሾች እንዲሰራላቸው በማድረግ፣ አጠቃላይ በድምሩ 2,985 ካ.ሜ ስፋት ያለው የመሬት ይዞታ ላይ ህገ-ወጥ መብት እንዲፈጠር በማድረግ የወቅታዊ የሊዝ መነሻ ዋጋውን መሰረት በማድረግ ሲሰላ በድምሩ 2 ሚሊዮን 643ሺ 432 ብር ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ፤ በ2ኛ ክስ በ8ኛ፣ 11ኛ እና ከ21ኛ እንዲሁም እስከ 40ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ባሉት ተከሳሾች የቀረበ ክስ ሲሆን ተከሳሾቹ እንደየስራ ኃላፊነታቸው በመንግስት ሰራተኝነት እንዲሁም የአርሶ አደር ኮሚቴ አባል ሆነው በልዩ ተካፋይነት በሚያገለግሉበት ወቅት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ቀኑና ወሩ ተለይቶ ባልታወቀ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በቀድሞ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 15 በአሁኑ ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኙ ይዞታዎች ላይ ሊያከናውኗቸው የሚገባቸውን ተግባራት ሳይፈፀሙ ኃላፊነታቸውን ወደ ጎን በመተው ከ28ኛ እስከ 41ኛ ተከሳሾች ጋር በጥቅም በመመሳጠር ያለ አግባብ የወረዳው አርሶ

ከሙስና ምርመራ... ወደ ገጽ 11 የዞረ

# ከሙስና ምርመራ...

አደር ናቸው በማለት ያለ አግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራላቸው በማድረግ ከ28ኛ እስከ 41ኛ ለተጠቀሱት ተከሳሾች አጠቃላይ በድምሩ 5,050 ካ.ሜ ስፋት ያለው የመሬት ይዞታ ላይ ያለ አግባብ መብት እንዲፈጠርላቸው በማድረግ የወቅታዊ የሊዝ መነሻ ዋጋውን መሰረት በማድርግ ሲሰላ 5 ሚሊዮን 425ሺ 669 ጉዳት እንዲደርስ በማድረግ፤

በ1ኛ እና በ2ኛ ክስ የተጠቀሱት ተከሳሾች በጥቅም በመመሳጠር በአካባቢው በነዋሪነትና በአርሶ-አደርነት የማይታወቁ፣ በይዞታዎቹ ላይ ቤት ገንብተው የማይኖሩና የማያስተዳድሩ ተከሳሾችን በአካባቢው ነዋሪ እና አርሶ-አደር እንደሆኑ፣ በይዞታዎቹ ላይ ቤት ሰርተው እየኖሩ እና እያስተዳደሩት እንደሆነ በማስመሰል ያለአግባብ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች ተዘጋጅተው እንዲሰጡ በማድረግ ውስን የሆነው የህዝብ ሀብት በፍትሀዊነት ጥቅም ላይ እንዳይውል ያደረጉ በመሆኑ ከላይ በተገለፀው የተሳትፎ ደረጃቸው ልክ የመንግስት ሰራተኛ ተከሳሾች በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆንና የመንግስት ሰራተኞች ሳይሆኑ በልዩ ወንጀል ተካፋይነት በፈፀሙት ስልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል፤ 3ኛ ክስ የቀረበው በ1ኛ፣ 11ኛ፣ ከ41ኛ እስከ 43ኛ ባሉት ተከሳሾች ላይ ሲሆን በህ-ወጥ መንገድ መብት የተፈጠረባቸው ይዞታዎች ሆነው እያሉ 22 ይዞታዎች የሚኙበትን የሚያሳይ ካርታ ተስተካክሎ እንዲዘጋጅላቸው በማለት ከፕሮሰስ ካውንስሉ ስልጣንና ሀላፊነት ውጭ በመወሰን ከላይ በ1ኛ ክስ ከ12ኛ እስከ 20ኛ ድረስ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የሚጠቅምና በመንግስት ላይ 2 ሚሊዮን 643 ሺ 432 ብር ያለአግባብ ጉዳት የሚያደርስና 2,985 ካ.ሜ ስፋት ያለው የመሬት ይዞታ ላይ ቀድሞ በህገ-ወጥ መንገድ የተፈጠረውን ህገ-ወጥ መብት የሚያፀና ውሳኔ በማስተላለፍ፤ ከላይ በ2ኛ ክስ ከ28ኛ እስከ 40ኛ ድረስ የተጠቀሱትን ተከሳሾች የሚጠቅም በመንግስት ላይ የብር 5 ሚሊዮን 425 ሺ 669 ብር ያለአግባብ ጉዳት የሚያደርስና 5,050 ካ.ሜ ስፋት ያለው የመሬት ይዞታ ላይ ቀድሞ በህገ-ወጥ መንገድ የተፈጠረውን ህገ-ወጥ መብት የሚያፀና ውሳኔ በማስተላለፍ፤

በአጠቃላይ ተከሳሾች በድምሩ በ8,035 ካ.ሜ ስፋት ያለው ይዞታ ላይ በህገ-ወጥ መንገድ የተፈጠረ መብትን በማፅናት በመንግስት ላይ በድምሩ 8 ሚሊዮን 69 ሺ 101 ብር ጉዳት ያደረሱ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በስልጣን ያለአግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባቸዋል::

ጉዳዩን የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ችሎትም ክሱን ለተከሳሾች በችሎት በማንበብ ተከሳሾች የክስ መቃወሚያ ካላቸው እንዲያቀርቡና ያልቀረቡ ተከሳሾችን ፖሊስ እንዲያቀርባቸው ለጥር 8 ቀን 2015 ዓ.ም ቀጠሮ መሰጠቱን መረዳት ችለናል::

በተጨማሪም በኢፌዲሪ ፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ስም 29 ሺህ 200 ኩንታል ሲሚንቶ ከሁለት ፋብሪካዎች ገዝተው ለግለሰቦች በመሸጥ፤ ከ30 ሚሊዩን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው ባዋሉ የአገልግሎቱ የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ም/ዳይሬክተርን ጨምሮ በአራት ሰራተኞች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው::

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተከሳሾች በብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ውስጥ 1ኛ ተስፋዬ ደሜ በብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ም/ዳይሬክተር፣ 2ኛ አሸናፊ ተስፋዬ የኮንስትራክሽን እና ሎጂስቲክስ ግዢ ዋና ክፍል ሃላፊ፣ 3ኛ ቱጅባ ቀልቤሳ እና 4ኛ ተከሳሽ ሙስጠፋ ሙሳ የግዢ ባለሙያ ሆነው ሲሰሩ መቆየታቸው ተጠቅሷል::

እነዚህ ግለሰቦች ተገቢ ያልሆ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በ2013 እና 2014 ዓ.ም በተለያዩ ወራት በብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ምንም አይነት ሲሚንቶ ግዢ ባልተፈፀመበት ሁኔታ በስሙ ሲሚንቶ ከፋብሪካዎች በአነስተኛ ዋጋ በመግዛትና ገበያ ላይ በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ህገ-ወጥ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በመስሪያ ቤቱ ስም ግዢ እንዲፈፀም እና ሲሚንቶው ወደ መስሪያ ቤቱ ገቢ ሳይደረግ አየር ላይ ተሽጦ ለግል ጥቅሙ እንዲውል አድርገዋል በሚል ክስ እንደተመሰረተባቸው ተገልጿል::

ተከሳሾች በጥቅም በመመሳጠር ምንም አይነት የግዢ ፍላጎት ሳይኖር በአገልግሎቱ ስም በፃፏቸው ደብዳቤዎች ከዳንጎቴ እና ደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች በድምሩ 29 ሺህ 200 ኩንታል ሲሚንቶ በመግዛት ወደ ተቋሙ ገቢ ሳያደርጉ ገበያ ላይ በመሸጥ 30 ሚሊዮን 99 ሺ 360 ብር ጥቅም ያገኙ በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት በስልጣን አላግባብ መገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰዋል ሲል ከፍትህ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

ተከሳሾች የተከሰሱበት ክስ በችሎት ደርሷቸው ክሱ የተነበበላቸው ሲሆን ተከሳሾችም የክስ መቃወሚያ ካላቸው በጽሁፍ እንዲያቀርቡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ወንጀል ችሎትም ለታህሳስ 7 ቀን 2015 ዓ.ም ትዕዛዝ መስጠቱን ለማወቅ ተችሏል::

በሌላ መረጃ በህገወጥ መንገድ በአርሶ አደርና በአርሶ አደር ልጅ ስም የይዞታ መብት በማጽናት የመንግስት ባዶ ቦታን በወሰዱ እና እንዲወሰድ ባደረጉ 21 ግለሰቦች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተ::

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ዋና ስራ አስፈፃሚን ጨምሮ በ21 ግለሰቦች በአርሶ አደርና በአርሶ አደር ልጅ ስም ለ11 ግለሰቦች ካርታ በማዘጋጀት 5 ሺህ 593 ካሬ ሜትር ይዞታን መብት በማፅናት እና አማካይ የሊዝ ዋጋው ከ11 ሚሊየን ብር የሆነ የመንግስት ባዶ ቦታን ወስደዋል እና እንዲወሰድ አድርገዋል በሚል ነው ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ የተመሰረተባቸው::

ክስ የተመሰረተባቸው ተከሳሾች የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መልካሙ በቃናን ጨምሮ ሌሎች በተለያየ የአመራርነት እና በባለሙያነት እያገለገሉ የሚገኙ ግለሰቦች ላይ ነው::

ግለሰቦቹ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በጥቅም በመመሳጠር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/2007 መሰረት የይዞታ ማረጋጋጫ የሚጠይቅ ሰው ማሟላት የሚገባውን መስፈርት ያላሟሉ፣ በህገወጥ መንገድ አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጅ ነን ያሉ 11 ግለሰቦችን የይዞታ ካርታ በማዘጋጀት አማካይ የሊዝ ዋጋው ከ11 ሚሊየን 900 ሺህ 67 ብር ከ31 ሳንቲም የሆነ የመንግስት ባዶ ቦታን በመስጠት፣ የካርታ መብት በማፅናት እንዲሁም 5 ሺህ 593 ካሬ ሜትር ይዞታን በህገወጥ መንገድ ወስደዋል ሲል ዐቃቤ ህግ በክሱ ዘርዝሯል።

በአጠቃላይ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1 ሀ እና የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9/1 ሀ እና ንዑስ ቁጥር 2 በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት እና በልዩ ወንጀል ተካፋይ በመሆን ስልጣንን ያለአግባብብ በመጠቀም በከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰዋል።

እንደ ኤፍቢሲ ዘገባ ከተከሳሾቹ መካከል የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ መልካሙ በቃና እና የክፍለ ከተማው የመሬት ማስከበር ጥበቃ ኦፊሰር ካርታ አረጋጋጭ ባለሙያ ገለታ ደበሌ ዛሬ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት በጽህፈት ቤት ከጠበቃቸው ጋር ቀርበው ክሱ እንዲደርሳቸው መደረጉን ኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት በድረ ገፁ በማስፈር ተመላክቷል።

በሌላ መረጃ በዳውሮ ዞን ከጪ ወረዳ ለመጀመሪያ ዙር ከተደረገው 264 የትምህርት መረጃ 127 ሀሰተኛ ሆኖ መገኘቱን የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ አቶ መላኩ ተረፈ ይፋ አድርገዋል።

ሀሰኛ ሆኖ ከተገኘው የትምህርት መረጃ መካከል 6ቱ የአመራርና ቀሪው የመንግስት ሰራተኞች እንደሆነ የገለፁ ዋና አስተዳዳሪው የሁለተኛ ዙሪ የማጥራት ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልና ውጤቱ በአጭር ጊዜ ለህብረተሰቡ ይፋ እንደሚደረግ አብራርተዋል።

ሀሰተኛ የትምህርት መረጃ በመንግስትና በህዝብ ሀብት ከፍተኛ ኪሳራ ከማድረሱም ባለፈ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሚያደርሰው መስተጓጎል በአከባቢው የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር እንደሚያደርግ ተነግሯል።

መላው የወረዳው ህዝብና የባለድርሻ አካላት መንግስት በየደረጃው ህገ ወጥ አሰራሮችንና ሌብነቶችን ለማስቀረት በሚያደርገው ጥረት ህብረተሰቡ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ ያቀረቡ ዋና አስተዳዳሪው የሀሰተኛ መረጃ የማጥራት ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አብራርተዋል።

በዳውሮ ዞን በሁሉም ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ህገ ወጥ አሰራሮችንና ሌብነትን በማስቀረጥ የዞኑን ብልፅግና ለማረጋገጥ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የዳውሮ ዞን የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ በግለሰቦች ጥቆማ መሰረት ፖሊስ ክትትል በማድረግ የመኖሪያ ቤት ዕድሳት ፈቃድ ለመስጠት ጉቦ የጠየቀ የወረዳ አስተዳደር ሰራተኛ 10 ሺህ ብር ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዞ ምርመራ እየተጣራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታወቀ።

ተጠርጣሪው ግለሰብ መርዕድ ከበበ ይባላል። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 10 አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ባለሙያ ነው። አቶ በድሉ አለማየሁ የተባሉት የግል ተበዳይ ቤታቸውን ለማደስ ፈልገው የእድሳት ፈቃድ ለማውጣት ወደ ወረዳው ቀርበው በጠየቁበት ወቅት ተጠርጣሪው ምክንያት እየፈጠረ በማመላለስ ማሳደሻ ፈቃዱን መውሰድ ከፈለጉ 10 ሺህ ብር እንዲሰጡት መጠየቁ ታውቋል።

የግል ተበዳይም ሁኔታውን ለፖሊስ በማሳወቅ እና ፖሊስም ክትትል በማድረግ ብሄረ ፅጌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መርዕድ ከበበ ከአቶ በድሉ አለማየሁ ላይ 10 ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዞ ምርመራ እየተጣራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል።

ሌብነትን ለመዋጋት የተጀመረው ሃገር አቀፍ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ህብረተሰቡ እያሳየ ያለው ተባባሪነት የሚያስመሰግን መሆኑን የጠቀሰው የአዲስ አበባ ፖሊስ፤ መረጃ እና ጥቆማ መስጠቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ መቅረቡን ኢቢሲ ዘግቧል።

በሌላ መረጃ በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ በተደረገ ክትትል የመኖሪያ ቤት ዕድሳት ፈቃድ ለመስጠት ጉቦ የጠየቀ የወረዳ አስተዳደር ሰራተኛ 10 ሺህ ብር ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዞ ምርመራ እየተጣራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታወቀ።

ተጠርጣሪው ግለሰብ መርዕድ ከበበ ይባላል።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የወረዳ 10 አስተዳደር የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ባለሙያ ነው። አቶ በድሉ አለማየሁ የተባሉት የግል ተበዳይ ቤታቸውን ለማደስ ፈልገው የእድሳት ፈቃድ ለማውጣት ወደ ወረዳው ቀርበው በጠየቁበት ወቅት ተጠርጣሪው ምክንያት እየፈጠረ በማመላለስ ማሳደሻ ፈቃዱን መውሰድ ከፈለጉ 10 ሺህ ብር እንዲሰጡት መጠየቁ ታውቋል።

የግል ተበዳይም ሁኔታውን ለፖሊስ በማሳወቅ እና ፖሊስም ክትትል በማድረግ ብሄረ ፅጌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መርዕድ ከበበ ከአቶ በድሉ አለማየሁ ላይ 10 ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዞ ምርመራ እየተጣራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል።

ሌብነትን ለመዋጋት የተጀመረው ሃገር አቀፍ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ህብረተሰቡ እያሳየ ያለው ተባባሪነት የሚያስመሰግን መሆኑን የጠቀሰው የአዲስ አበባ ፖሊስ፤ መረጃ እና ጥቆማ መስጠቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ መቅረቡን ኢቢሲ ዘግቧል።

በአዲስ አበባ ሃሰተኛ የነዋሪነት መታወቂያ እያዘጋጁ ሲሸጡ የነበሩ 3 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር ዋሉ::

በተጨማሪም በዳዉሮ ዞን የሀሰተኛ ትምህርት ማስረጃ የማጣራትና በኦዲት ግኝት ተገኘውን መንግሥትና የህዝብ ሀብት ለማስመለስ የሚያስችል ተግባር በተቀናጀ ጥረት ሕግ የማስከበር ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ የዞኑ ፍትሕ መምሪያ አስታወቀ::

የህግ የበላይነትን ለማስከበር እየተደረገ ባለው ጥረት የህብረተሰቡ ቀና ትብብር እንደሚያስፈልግ የዞን ዋና አስተዳደሪ ገልፀዋል::

በዞኑ ማረቃ ወረዳና ተርጫ ከተማ አስተዳደር ከ8.5 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነውን በኦዲት ግኝት የተገኘውን ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ለማስመለስ በተግባሩ የተጠረጠሩ 22 ግለሰቦች ላይ ክስ መመስረቱም ተገልጿል::

በዳውሮ ዞን በተያዘው በጀት ዓመት ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ፣ ከሌብነትና ከሙስና ወንጀል ጋር የተያያዙ የአሠራር ጥሰት በማረም የሕግ ማስከበር ሥራ በተቀናጀ ጥረት እየተከናወነ ይገኛል::

በተለይም አሁን ላይ ከሙስና ወንጀልና ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ማጥራት ጋር ሂደቱ ውስብስብ በመሆኑ ተግባሩ በትኩረት እየተከናወነ እንደሚገኝ በዞኑ ፍትሕ መምሪያ የሙስና ወንጀሎች ምርምራ ዐቃቤ ሕግ አቶ አሰግድ ታከለ ተናግረዋል::

የዞኑ ፍትሕ መምሪያ ኃላፊ አቶ ፈለቀ ከበደ በበኩላቸው በዞኑ ማረቃ ወረዳ ከመንግስት ፋይናንስ ጋር እና ከታርጫ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በኦዲት የተገኘው ከ8.5 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነውን ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ለማስመለስ እየተሰራ ነው ብለዋል ::

በማረቃ ወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት በቼክ ማጭበርበር እና በታርጫ ከተማ አስተዳደር ከገንዘብ ብክነት ጋር በተገናኘ በተግባሩ የተጠረጠሩ 22 ግለሰቦች ላይ ክስ መጀመሩን ገልጸዋል::

የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ደስታ ደምሴ በበኩላቸው የትምህርት ማስረጃዎችን በማጣራት ሂደትም ሆነ የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ተግባራት በትኩረት እየተከናወኑ በመሆናቸው፣ ተግባሩ ከውጤት እንዲደርስ የህብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑንም ማስረዳታቸውን ከደቡብ ብብሀክልል የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ የተገኘው ማስረጃ ያመለክታል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ኪነ-ጥበብ

**መኖር ማለት አለመሞት ከሆነ፣**
**እስትንፋስ ያለው ሁሉ**
**እየኖረ ነው፡፡**
**ግን መኖር ማለት**
**ራስን መሆን፣**
**ለአላማ መቆም፣**
**ህሊናን አለመዘንጋት፣**
**ፍርድ አለማጓደል፣**
**ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌላው ራስን**
**መሰዋዕት ማድረግ፣ ብሎም**
**አርዕያ**
**የሚሆን ነገር ጥሎ ማለፍ ከሆነ፣**
**ስቶቻችን ነን**
**በህይወት ያለነው????**

**ዶ/ር ምህረት ደበበ**

# መልካም ዜጋ

## ከአትሌቲክስ ትራክ እስከ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንትነት የዘለቀው የአትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ስኬት




ከኢትዮጵያም አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በረጅም ርቀት ተደናቂ ከሆኑት ሴት አትሌቶች አንዷ ነች። ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ አርሲ ውስጥ በቆጂ በተባለ አካባቢ በ1965 ዓ.ም ተወለደች። ደራርቱ ስፖርታዊ ውድድር ማድረግ የጀመረችው ገና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ በነበረችበት ጊዜ እንደነበር ታሪኳ ያስረዳል።

ደራርቱ ወደ መጨረሻው የትምህርት ቤቷ የቆይታ ዘመን ትምህርት ቤቷን እየወከለች በ800 እና በ1500 ሜትር ርቀቶች እየተወዳደረች በተደጋጋሚ መልካም ውጤቶችን አስመዝግባለች። በትምህርት ቤት ውድድሮች ታዋቂነትን እያገኘች እንደመጣች በ1980 ዓ.ም የማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክለብ አባል ሆነች።

በ1981 ዓ.ም ኖርዌይ ስታቬንጋር ከተማ በተካሄደው 17ኛው የአለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ላይ በስድስት ኪሎ ሜትር የመጀመሪያውን ዓለም አቀፍ ውድድር በማድረግ 23ኛ ደረጃ መውጣቷ ይነገራል። በቀጣዩ ዓመት በተመሳሳይ ርቀት በፈረንሣይ ተወዳድራ የአንደኛነት ደረጃን አገኘች። በዚያው ዓመት ቡልጋሪያ ላይ በተካሄደው የ10ሺህ ሜትር ውድድር አሁንም አንደኛ ሆና በበላይነት በመጨረስ በረጅም ርቀት ሩጫ ዘርፍ ወደፊት የመምጣት ጅማሬዋ ነበር።

ኮማንደር ደራርቱ በ1984 ዓ.ም በስፔን በባርሴሎና ተዘጋጅቶ በነበረው ኦሎምፒክ በ10ሺህ ሜትር ተወዳድራ ድል አስመዝግባ ወደአገሯ እንደተመለሰች የሻለቃነት ማዕረግ አግኝታለች። ደራርቱ ስለ ባርሴሎና ኦሎምፒክ ስትናገር፣ "የባርሴሎና ኦሎምፒክ የሕይወቴን አቅጣጫ የቀየረ ነበር። ከአስራ አለቃነት ወደ ሻለቃነት ደረጃ አደግኩኝ፤ ደሞዜ ከ200 ብር ወደ 600 ብር አደገ፤ ዝናዬም ናኘ" ስትል ድሉ ያመጣላትን በረከት ትናገራለች።

በባርሴሎናው ኦሎምፒክ ያገኘችው የወርቅ ሜዳሊያ የእርሷ እና የሀገሯ ብቻ ሳይሆን የመላ ጥቁር ህዝቦች ድልም ነበር። ከዚህ የደራርቱ ድል በኋላም በእርሷ አሸናፊነት መንፈስ የተቃኙ በርካታ ሴት ኢትዮጵያዊያን ሯጮች ለመታየት በቅተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ደራርቱ በ37 አመቷ የኒውዮርክ ማራቶንን ማሸነፍ የቻለች ምርጥ እና ፋና ወጊ ኢትዮጵያዊ አትሌት ነች።

ኮማንደር ደራርቱ በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ በርካታ ሜዳለያዎችን አግኝታለች። በ1993 ዓ.ም በአውስትራሊያው የሲድኒ ኦሎምፒክ ላይም በተለመደው የ10ሺህ ሜትር ርቀት ተወዳድራ የወርቅ ሜዳለያ ተሸላሚ ሆናለች።

አትሌት ደራርቱ ቱሉ፡-

- በተለያዩ ኦሎምፒኮች
- በዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች
- በዓለም አገር አቋራጭ ውድድሮች
- በኮንቲኔንታል ካፕ
- ከ20 ዓመት በታች የዓለም ሻምፒዮና
- በአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች
- በዓለም አትሌቲክስ
- በጎልደን ሊግ
- በዓለም አቀፍ ማራቶን
- በኢትዮጵያ አትሌቲክሰ ሻምፒዮናዎች

አጠቃላይ ከ13 በላይ ወርቆች፣ 2 ብሮች፣ የነሃስ ሜዳሊያ እና 3 ዲፕሎማዎችን ለሃገሯ ኢትዮጵያ አበርክታለች።

የኮማንደር ደራርቱ ቱሉን ፈለግ በመከተል በ10ሺህ እና በ5ሺ ሜትር ርቀቶች ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡ ሴት አትሌቶች መካከል አትሌት ጌጤ ዋሚ፣ ጥሩነሽ ዲባባ እና መሰረት ደፋር እንዲሁም ለተሰንበት ግዳይ ተጠቃሾች ናቸው።

አሁን ላይ ደራርቱ በአዲስ አበባ እና አዳማ ከተሞች በሆቴል እና የንግድ ህንፃ ግንባታ ተሰማርታ ትገኛለች። አትሌቷ ስለ አሁናዊ ሁኔታዋ ስትናገር፣ "ከአትሌቲክስ ባፈራሁት ገንዘብ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራሁ ነው፤ ራሴንና ቤተሰቤን ከመርዳት አልፌ ማለት ነው። በርካታ የሥራ ዕድል በመፍጠር ለሃገሪቱ ዕድገት የበኩሌን አስተዋፅኦ እያበረከትኩ ነው" በማለት ትናግራለች።

አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በአትሌቲክስ ህይወቷ ላበረከተችው አስተዋጽኦ የተለያየ ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ሽልማቶችንም አግኝታለች።

- ከደቡብ አፍሪካው ዌስተርን ኬፕታውን ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት፣
- በጣልያን በተካሄደ ዓለም አቀፍ ሽልማት የህይወት ዘመን የስፖርታዊ ጨዋነት ዘርፍ ተሸላሚ፣
- የመጀመሪዋ ሴት አፍሪካዊት በ10 ሺህ ሜትር የኦሎምፒክ የወርቅ አሸናፊ አትሌት፣
- በአዳማ የሚገኘውን ትልቁ አደባባይን በኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ተሰይሟል።
- በአዲስ አበባ ከተማ ሀያት አካባባቢ የሚገኘው የሀያት አደባባይ በስሟ ተሰይሟል።
- በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም 350 ግራም የወርቅ ኒሻን እንዲሁም የ2021 ሞዴል የሆነች ሌክሰስ ቪ8 መኪና ከኦሮሚያ ክልል ተበርክቶላታል።

አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በአሁኑ ጊዜ የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል፣ የምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ዞን ምክትል ፕሬዝዳንትነት፣ የምሥራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ የአካባቢው ምክትል ፕሬዚዳንት ሆና እያገለገለች ትገኛለች።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት ሆና በማገልገል ላይ የምትገኘው አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስራ አስፈፃሚም አባል ነች።

ደራርቱ በአትሌትነት ዘመኗ አፍሪካዊያን ጭምር ብዙ ገፍተው ባልወጡበት የረጅም ርቀት ውድድር ፈንጥቃ በመውጣት ከሷ በኋላ ለመጡ ሴት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችም ፈር ቀዳለች። ከአትሌትነት ወደ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ፕሬዝዳትነት ስትመጣም ኢትዮጵያ በአለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ታሪክ ከፍተኛውን 4ወርቅ ጨምሮ በ10 አጠቃላይ ሜዳሊያ ኢትዮጵያ ወደ ስኬት ጫፍ እንድትደርስ ሚናዋን ተጫውታለች።

ኢትዮጵያ በ18ኛው የኦሪገኑ የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከዓለም አሜሪካን ተከትላ በ2ኛነት እንዲሁም ከአፍሪካ ደግሞ በ1ኛነት በማጠናቀቅ ለተገኘው ድል የደራርቱ አመራርነት ሚና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን በርካቶች ምስክርነታቸውን እየሰጡ ነው። በሻምፒዮናው ላይ አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ከአመራርነት ሚናዋ ባሻገር ለአትሌቲክስ ቡድኑ እና ለአትሌቶቹ የእናትነት ሚናዋን በማሳየት ጭምር ኢትዮጵያ ከፍ ላለ ድል እንድትበቃ አድርጓል የሚል አስተያየት ሰጪዎች ብዙ ናቸው።

አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ስኬቷ ከአትሌቲክስ መም (track) እስከ አመራረነት የዘለቀ ነው በሚል ትውልድ ከፍ አድርጎ እንዲዘክረው ተደርጎ የተጻፈው አበርክቶዋ አገራዊ ምልክትነቱ እና አርዓያነቱ በጉልህ ቀለም የተጻፈ ታሪክ እንዲሆን አድርጎታል።

**በሻምፒዮናው ላይ አትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ከአመራርነት ሚናዋ ባሻገር ለአትሌቲክስ ቡድኑ እና ለአትሌቶቹ የእናትነት ሚናዋን በማሳየት ጭምር ኢትዮጵያ ከፍ ላለ ድል እንድትበቃ አድርጓል የሚል አስተያየት ሰጪዎች ብዙ ናቸው**